# 🌿🌿🌿 ሦስተኛ ዙር የጥያቄዎች መልስ 🌿🌿🌿




**አዘጋጅ፡- በትረማርያም አበባው ካሣ**

**(የመጻሕፍተ ብሉያት፣ የመጻሕፍተ ሊቃውንትና የመጻሕፍተ መነኰሳት ትርጓሜ መምህር)**


**ግንቦት ፳፮፣ ፳፻፲፫ ዓ.ም**

## ሦስተኛ ዙር የጥያቄዎች መልስ

፩. የወንድ የጸጉር አቆራረጥ ምን መሆን አለበት አንዱን ክፍል ከፍ ሌላውን ዝቅ አድርጎ መቆረጥ ይቻላል ወይ? ጸጉርና ጺም አንድ ላይ መቆረጥ አይቻልም የሚባለውስ እንዴት ነው?

መልስ፦ ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 51 ላይ እንደተገለጸው ወንድ ልጅ ጸጕሩን አያሳድግ ተብሏል። "ኢይኅድግ ብእሲ ሥዕርቶ ከመ ይኑኅ ለግሙራ" እንዲል። ይህ ብቻ ሳይሆን ሲላጭም ጋሜ፣ ቁንጮ እያለ ግማሹን ተላጭቶ ግማሹን መተው ወይም ደግሞ ከፍና ዝቅ አድርጎ መላጨት እንደሌለበት ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 45 ላይ ተገልጿል። "ወኢትላጺ መንፈ*ቀ ሥዕርተ ርእስከ" እንዲል።

፪. የቅዱስ ራጉኤል ሥዕል ላይ ያሉት አንድ አካል ሦስት ጭንቅላት ያላቸው ወፎች ምንድን ናቸው?

መልስ፦ አላውቃቸውም። ምናልባት ሥዕላት ሲሣሉ ድርሳኑን መሠረት አድርገው ስለሚሣሉ ከድርሳኑ ታሪካቸው ተገልጾ ከሆነ ብታዩት።

፫. አካል ለሥላሴ እንዴት ይተረጎማል ተብሎ ለተጠየቀው ጥያቄ ወሰን የሌለበት ረቂቅ አካል ነው ብለው ነበር። እና ወልድ በሚታይ በሚዳሰስ ሥጋ መገለጡስ እንዴት ይነገራል?

መልስ፦ ወልድ በተለየ አካሉ ሥጋን በመዋሐዱ በተዋሐደው ሥጋ ወሰን ያለበት፣ የሚዳሰስ ነው። አብና መንፈስ ቅዱስ ግን ሰው ስላልሆኑ ረቂቅ አካልነታቸው ብቻ ይነገራል። ለወልድ ግን ርቀትም ግዝፈትም፣ ምልዐትም ውሱንነትም በተዋሕዶ ገንዘቡ ነው።

፬. አንድ ዲያቆን ከዲቁናው በፊት ከሴት ጋር በ10 ዓመቱ ግንኙነት ያደርጋል። ከዚያ ካደገ በኋላ ንስሓ ገብቶበት ንስሓ አባቱን ዲቁና መቀበል ይችል እንደሆነ ሲጠይቅ ፈቀዱለት። እና ልጁ ንስሓ ገብቶ ንስሓ አባቱ ፈቅደውለት ቢሆንም ኅሊናው አንዳንዴ ይበጠብጠዋል። ከሥርዓተ እግዚአብሔር አንጻር እንዴት ይታያል?

መልስ፦ ከሰባት ዓመት በኋላ ሥርዓት ለሁሉ የሚተገበር ነው። ስለዚህ ይህ ሰው 10 ዓመቱ ላይ ዝሙትን ፈጽሞ ከነበረ ዲቁና መቀበል አይገባውም ነበር። የተማረ ንስሓ አባት ያዙ የሚባል እንደዚህ ያለ ስሕተት እንዳይፈጸም ነበር። ግንኙነት ካደረገ አደረገ ነው። ጉዳዩ ዘር ከመፍሰስ ካለመፍሰስ ጋር ሳይሆን የሚታይ ግንኙነት መፈጸም ካለመፈጸም ጋር ነውና። ስለዚህ ክህነቱን የተቀበለባቸውን ጳጳስ ሄዶ ያደረገው የነበረውን ይንገራቸውና መፍትሔ ይስጡት።

፫. መንፈስ ቅዱስን ለመቀበል ከአንብሮተ እድ ወደ ቅብዓ ሜሮን የተቀየረው በምን ምክንያት ነበር? አንብሮተ እድን የሚፈጽሙትስ ጳጳሳት ብቻ ነበሩ ቀሳውስት መፈጸም አይችሉም ነበር?

መልስ፦ በምን ምክንያት እንደተቀየረና ከመቼ ጀምሮ እንደጀመረ ምንም ዓይነት ታሪካዊ ማስረጃ የለኝም። አላውቀውም። እስኪ የቤተክርስቲያንን ታሪክ በጥልቀት ያጠኑ ሰዎችን ጠይቁ።

፬. የቅዳሴ ጠበል እና ማየ መቍርር አንድ ናቸው? ከሆኑ ከቅዳሴ ጠበል ውጭ ሌላ ጠበል በቤተክርስቲያን ባይኖር ያልቆረበ ሰው ሳይጠጣ ነው መመለስ ያለበት?

መልስ፦ ማየ መቍርር የሚባለው በሌላ አገላለጽ የቅዳሴ ጠበል የሚባለው ነው። ማየ መቍርር ለቆረቡ ሰዎች ብቻ የሚሰጥ ነው። ላልቆረቡ ሰዎች የሚሰጠው ከመቅደሱ ውጭ በቅኔ ማኅሌቱ የነበረ ሌላ ጠበል ነው። መቅደስ ውስጥ ከነበረው ከማየ መቍርር ውጭ ሌላ ከሌለና ካልቆረቡ ዝም ብሎ የሰንበት ቂጣውን በልቶ መመለስ ነው።

፭. አምላክም ሰውም፣ አምላክና ሰው፣ ሰው የሆነ አምላክ አምላክ የሆነ ሰው የሚሉት ሐረጋት ልዩነቶቻቸው ምንድን ነው?

መልስ፦ አምላክም ሰውም የሚለው ለአንድ አካል ለአንድ ባሕርይ የሚነገር ነው። ያ አንዱ አካል አምላክም ነው ሰውም ነው ማለት ነው። አምላክና ሰው የሚለው አገላለጽ ግን ለሁለት አካል ለሁለት ባሕርይ የሚነገር ነው። ሰው የሆነ አምላክ አምላክ የሆነ ሰው የሚለው የቃልንና የሥጋን ተዋሕዶ የሚያሳውቅ ነው። በጊዜ ተዋሕዶ ቃል ሥጋን ስለሆነ ሰው የሆነ አምላክ ይባላል። በዚያው ቅጽበት ያለመቀዳደም ሥጋም ቃልን ሆኗልና አምላክ የሆነ ሰው ይባላል። ሰማይ ኮነ ዓለመ ወዓለም ሰማየ እንዳለ ሊቁ።

፮. ከአንጾኪያ እና ከእስክንድርያ ትርጓሜ ስልቶች የሚቀድም ትርጓሜ አለ?

መልስ፦ አዎ አለ። የሁለቱም ትርጓሜዎች መሠረት የጌታችን የመድኀኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ትርጓሜ ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ እንደተገለጸው ለሐዋርያት ለሕዝቡ እየተረጎመ ያስተምራቸው ነበርና።

፯. በእኛ ቤተ ክርስቲያን ቅዳሜ መከበር የጀመረው በአጼ ዘርዓ ያዕቆብ ነው ይላሉ። እስከዚያ አልተከበረችም?

መልስ፦ በዚህ ዙሪያ ምንም ታሪካዊ ግንዛቤ የለኝም አላውቀውም። ነገር ግን ሰንበትን [ቅዳሜን] አክብሩ የሚለው ያልተሻረ ሕግና ከዐሥሩ ትእዛዛት አንዱ ስለሆነ በኢትዮጵያ

ክርስትና ከዚያ በፊትም ከነበረ ክርስትና ያለሕገጋት ስለማይሆን እስከዚያ አልተከበረችም የሚለው እይታ ብዙም የሚዋጥ አይደለም፡፡

፲. ጴጥሮስ ሁሉን ትተን ተከተልንህ ይላል፡፡ ሚስቱን ትቷል ወይስ አልተዋትም (1ኛ ቆሮ.9፥5)?

መልስ፦ ቅዱስ ጴጥሮስ ሁሉን ትተን ተከተልንህ ማለቱ እከብር ባይ ልቡናን ትተን ተከተልንህ ማለት ነው እንጂ ሚስትን ስለመተው አያመለክትም፡፡ 1ኛ ቆሮ.9፥5 ላይም ጴጥሮስ ሚስቱን አስከትሎ እንደነበር ተገልጿል፡፡ ከዚህ ውጭ ስለነበረው ሁኔታ ግን የሚገልጽ ነገር አላገኘሁም፡፡

፲፩. በተለያየ ጊዜ ሁለት አባቶች ቡራኬ ሲሰጡ "እመቤታችን ተማልዳ ታማልደን" ሲሉ ሰማሁ ምን ማለት ነው?

መልስ፦ ይህ አማርኛ መነሻው የት እንደሆነ አላውቀውም፡፡ ሐሳቡ ግን እርሷ የእኛን ልመና ተቀብላ ጌታ ደግሞ የእርሷን ምልጃ ተቀብሎ ያድነን ይማረን ማለት ነው፡፡

፲፪. ጸሎት ስንጸልይ ከልባችን በተመስጦ ለመጸለይ ምን ማድረግ አለብን? እኔ ከራሴ ጀምሮ በጸሎት ጊዜ ሁልጊዜም ሌላ ሐሳብ ይመጣብኛል፡፡ በቃ ምን እዳልኩ ሳላውቀው እጨርሰዋለሁ፡፡ እየጸለይኩ ሌላውን ሐሳብ ነው የማስኬደው፡፡ በጸሎትም ብቻ ሳይሆን ሌላም መንፈሳዊ መጽሐፍም ሳነብ ሌላ ሐሳብ ይመጣብኛል፡፡ ትኩረት ሰጥቶ ለማንበብ እና ለመጸለይ ዘለቂው መፍትሔ ምን ማድረግ አለበኝ?

መልስ፦ ይህ የብዙዎቻችን ችግር ነው፡፡ ሐሳባችን ሳይበታተን ጸሎትን በተመስጦ ለመጸለይ ግን ብናደርገው ብዬ የማስበው ዓለም ላይ ካሉት ነገሮች ሁሉ የሚበልጠው፣ ከጉዳዮች ሁሉ የሚበልጠውና ለእኛ ከምንም በላይ ትልቁ ጊዜ ከፈጣሪ ጋር መነጋገር መሆኑን ማሰብ ነው፡፡ መንፈሳዊ መጻሕፍትን ማንበብም ወደ እግዚአብሔር የሚያደርስ ስለሆነ ምሥጢሩን እያስተዋልን ማንበብና ሌላው የመጣብን ሐሳብ ግን ምንም ጥቅም የሌለውና ውድ ጊዜያችንን የሚያባክንብን መሆኑን መረዳት ነው፡፡

፲፫. ሐዋርያው ናትናኤል ሰማዕት የሆነ ሐምሌ 10 ነው ወይስ ግንቦት 15?

መልስ፦ ከ12ቱ ሐዋርያት አንዱ የሆነው ናትናኤል (ስምዖን ቀነናዊ/ቃናዊ) ሰማዕትነቱን የፈጸመው ግንቦት 15 ቀን ነው፡፡ ሐምሌ 10 የሚከበረው ስምዖን ቀለዮጳ የሚባለው ሌላ ቅዱስ ነው፡፡

፲፬. ቅዱስ ቊርባን እንደ ዛሬ የተቀበለ ሰው ለነገ በጠዋት ቤተ ክርስቲያን ጸሎት ለማድረግ ሲሄድ ፊቱን ታጥቦ መሄድ ይገባል?

መልስ፦ ቊርባን ከተቀበለበት ጊዜ ጀምሮ 24:00 ሰዓት እስኪሞላው ድረስ መታጠብ የለበትም። አንድ ቀን (24:00 ሰዓት) ከሞላው በኋላ ከሆነ ግን ታጥቦ ወደ ቤተክርስቲያን መግባት ይችላል። ይህ ሰዓት ካልሞላ እንዲሁ ወደቤተ ክርስቲያን መሄድ ነው።

፲፭. ከመዝሙረ ዳዊት በየቀኑ አንድ ንጉሥ ብቻ ማድረስ ይቻላል?

መልስ፦ የቻለ የየዕለቱን መድገም ነው። ይህ የሚበዛበትና የሚሰለቸው ካለ ደግሞ እንደ አቅሙ አንድ ንጉሥም እየጸለየ መኖር ይችላል። ፍሬ ነገሩ መጸለዩ ላይ ነው።

፲፮. የዐቢይ ጾም አቆጣጠሩ እንዴት ነው? ለምሳሌ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የጾመው 40 ቀንና 40 ሌሊት ነው። እኛ የምንጾመው ዐቢይ ጾም እንዴት ነው 40 የሚሞላው?

መልስ፦ ሠለስቱ ምእት በፍትሐ ነገሥት ቅዳሜና እሑድ እንደሌሎች ዕለቶች ቀኑን ሙሉ በመዋል መጾም የለባቸውም ብለው ሥርዓት ሠርተውልናል። ስለዚህ ቅዳሜንና እሑድን ትተን ስንቆጥረው 40 ቀን ስለሚሆን ጌታ ከጾመው ጋር ይመሳሰላል። በነገራችን ላይ ጌታ 40ውንም ቀን ሁሉ ምንም ምግብ አልቀመሰም። ሁሉንም እንደእርሱ እናድርግ ብንል አንችልም። አርባ ቀን ሙሉ ምንም ምግብ ሳይቀምስ ቢኖር ሰው ይሞታልና። ስለዚህ እኛ ውለን በመብላት እንጾማለን።

፲፯. ልብስን በተመለከተ የጻድቃን የመላእክት ምስል ወይም ጽሑፍ ያለው ልብስ ይለበሳል? ይለበሳል ከሆነ መጨረሻው ሲያርጅ ወደ ቆሻሻ እየተጣለ ነው እንዴት ነው?

መልስ፦ በዚህ ዙሪያ የተሠራ ሥርዓት አላገኘሁም። ነገር ግን ሥዕላት ቅዱሳት እንደመሆናቸው በልብሳችን ከምናሠራቸው ይልቅ ከንጹሕ ቦታ ተቀምጠው ብንጸልይባቸው ይመረጣል። ቅዱሳት ሥዕላት ደግሞ ምንም ያህል ቢያረጁ በክብር ይቀመጣሉ እንጂ ወደቆሻሻ አይጣሉም።

፲፰. በንግሥ በዓል ታቦት ሲዞር ሴቶች ምእመናን ይዞራሉ አይዞሩም? ይዞራሉ ከሆነ ቤተልሔም አከባቢ እንዴት ያደርጋሉ?

መልስ፦ በዚህ ዙሪያ የሚፈቅድም የሚከለክልም ሥርዓት ወይም ትውፊት አላየሁም። ግላዊ አስተያየቴ ግን በንግሥ ጊዜ ሁሉም እግዚአብሔርን እያመሰገነ ቢዞር ችግር የለውም ባይ ነኝ።

፲፱. ሰንደል ከቤተክርስቲያን ወይም ከቤት ማጨስ ይቻላል ወይም አይቻልም?

መልስ፦ ከቤተክርስቲያን እንዲጨስ ሥርዓት የተሠራው ዕጣን ነው እንጂ ሌላ ነገር እንድናጨስ አልተፈቀደም። ስለዚህ ሰንደል አይጨስም። ከቤታችን ግን ሌላ ባዕድ

አምልኮ ካልጨመርንበት መዓዛው ደስ የሚል ሰንደልንም ሌላም የጭስ ዓይነት ቢኖር ማጨስ እንችላለን፡፡

፰. አንድ ተሳዳቢ የሆነ ሰው ንስሐ ለመግባት ቢፈልግ ተሳድብያለሁ ነው ብሎ መናዘዝ ያለበት ወይስ የተሳደበውን ዘርዝሮ ነው የሚናገረው? ስድቡ አልታወስህ ቢለውስ ምን ያደርጋል?

መልስ፦ በተቻለው መጠን የተሳደበውን ስድብ ያስታወሰውን በዝርዝር ተናግሮ ንስሓ ቢገባ መልካም ነው፡፡ ካላስታወሰው ግን ያስታወሰውን ይግባበትና ባላስታወሰው ደግሞ እግዚአብሔር ይቅር እንዲለው እየጠየቀ ቀጣይ ይህንን በደል ላለመበደል ተጠንቅቆ መኖር ነው፡፡

፰፩. እኔ ከልጅነቴ ጀምሮ ዲቁናዉን በጎን የሳይንስ ትምህርቱንም በጎን እማራለሁ የሚል አሳብም ፍላጎትም ነበረኝ፡፡ ከዚያም እንዳሰብኩ አልቀረሁም ጎን በጎን ሁሉንም ጀመርኩኝ፡፡ ነገር ግን ብጀምርም እንኳን በጊዜዉ ማለትም የ6ኛ ክፍል ተማሪ ሆኜ ሳለ በሰው ቤት ነበር እና የምኖረው በሰዓቱ ከሴት ጋር ዝሙት ፈጸምኩኝ፡፡ ይሄም ብቻ አደለም ግብረ አውናንም በጣም ይፈታተነኛል እስካሁንም እየፈጸምኩ እገኛለሁ፡፡ ከዚያ ዲቁና ለመቀበል ስፈተን ስላላለፍኩ ሰው እንዲፈተንልኝ አደረኩና ቡራኬውን አብሬ ገብቼ ተባርኬ ዲቁና ካርዱን አመጣሁ፡፡ ይህ በደል መሆኑን አውቄ አሁን የአእምሮ ዕረፍት አጥቻለሁ፡፡ አሁን በዲቁናየ ልቀጥል? የዲቁና ወረቀቱንስ ምን ላድርገው ልቀጥል? እስካሁን ድረስ ከሚፈታተነኝ የዝሙት መንፈስ እና የግብረ አውናን የዝሙት መንፈስስ እንዴት ልላቀቅ? እጮኛ ነበረችኝ ዲቁና እንዳለኝም ታቃለች እና ወደፊት ሳገባህ በተክሊል ነው አለች፡፡ አኔ ደግሞ አሁን አልማርም ትቸዋለሁ አልኳት ለምን ስትለኝ ከላይ ያለውን ሙሉ እውነታ ከነማስረጃዉ ሳልነግራት ቀረሁ፡፡ በጣም ስለምወዳት እርሷም ከእኔ መራቅ አትፈልግም እና በዚህ ምክንያት ባትረዳኝስ ልትከዳኝ ልትርቀኝስ አይደለም ወይ አልኩ፡፡ ታዲያ እኔ እርሷን እሽ ብዬ ነው በተክሊል ማግባት ያለብኝ ወይስ እሷን መራቅ ነው ያለብኝ? ወይስ ምን ላድርግ?

መልስ፦ በመሠረቱ ሰው ሰባት ዓመት ከሆነው በኋላ ዝሙት ከፈጸመ ዲቁና መቀበል አይችልም፡፡ ዲያቆን የሚሆን ሰው በድንግልና ጸንቶ የኖረ ከዚያም ድንግል የሆነችትን የሚያገባ እንደሆነ ከዚህ ቀደም መጽሐፈ ሐዊን ጠቅሰን ተማምረናል፡፡ የዲቁና ፈተናውን ማለፍ ስላልቻልክ አጭበርብረህ ቡራኬውንም የዲቁና ወረቀቱንም መቀበልህም ልክ አይደለም፡፡ ስለዚህ ይህንን ዲቁና የተቀበልክባቸውን ሊቀ ጳጳስ ያደረግከውን ንገራቸውና እርሳቸው የሚሉህን አድርግ፡፡ ምንም እንኳ ያደረግከው ድርጊት ትልቅ ስሕተት ቢሆንም እግዚአብሔር ግን አንድ ጊዜ ባጠፋነው ጥፋት ምክንያት ጠፍተን እንድንቀር አላደረገንም፡፡ ስለዚህ የጥፋተኝነት ስሜት ከተሰማህ ይህ በራሱ የንስሓ መጀመሪያ ስለሆነ ጥሩ ነው፡፡ ስለዚህ እግዚአብሔር በደልህን ይቅር ይልህ ዘንድ ንስሓ ገብተህ ከኃጢአት ማሰሪያ ነጻ ሆነህ ለወደፊቱ ላለመበደል ቁርጥ

ኀሊናን ይዘህ በደስታ መኖር ትችላለህ:: ለልጂቱም ግልጹን ነግረሀት አንድ ላይ መፍትሔ መፈለግ አለባችሁ እንጂ ዋሽተህ በተክሊል ማግባት የለብህም:: መዋደዱ ካለ አንተ ያለ ተክሊል በቁርባን እርሷ ደግሞ ድንግል ከሆነች በተክሊል ማግባት ትችላላችሁ:: ፍትሐ ነገሥት ይህንን ያዝዛልና:: ከግብረ አውናን ለመላቀቅ ደግሞ መጾም፣ መጸለይ፣ እንቅልፍ መቀነስ፣ ምግብ መቀነስ መልካም እንደሆነ መጽሐፈ መነኰሳት ይነግረናል:: በተጨማሪም ሞትን፣ የገሃነምን መራራነት፣ የመንግሥተ ሰማያትን ዘለዓለማዊ ደስታ ማሰብ ነው:: ጌታችን መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስለእኛ በመስቀል መሰቀሉን ማሰብም ለዚህ ጥሩ መድኀኒት ነው::

፳፪. ሁለት ካህናቶች በግብረ ሰላም ጥሪ ሄደው በግል አለመግባባት ፈጥረው ተጣሉ:: እና በሰበካ ጉባኤ ተከሰው ሰበካ ጉባኤው የራሱን ውሳኔ የሰጠ ሲሆን እርሱም ከቤተ ክርስቲያን ከማንኛውም አገልግሎት ለአንድ ወር የታገዱ ሲሆን ከዚህ እግድ ውስጥ ግን መስቀል ማሳለምም አትችሉም ተባሉ:: እና ወረዳ ቤተ ክህነቱም አጽድቂዋለሁ አለ:: ዋናው ጥያቄዬ ሰበካ ጉባኤውም ይሁን ወረዳ ቤተ ክህነቱ መስቀል ካህን እንዳያሳልም ለጊዜው መከልከል ይችላል? ይችላል ከተባለ በቃለ ዓዋዲው አንቀጽ 63፥1-3 ያለው ኀይለ ቃል ምን ለማለት ነው?

መልስ፦ መቼም ሰው ደካማ ስለሆነ እርስ በእርሱ ሊጣላ ይችላል:: እነዚህ ቀሳውስትም ቀን ጥሏቸው ተጣልተዋል:: ሰበካ ጉባኤው ለአንድ ወር ከአገልግሎት ማገዱ መልካም ነው:: ወረዳ ቤተክህነቱ ማጽደቁም ጥሩ ነው:: ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 9 ላይ "ካህን ከሚመስለው ካህን ጋር ቢጣሉ ይሰደዱ ክልኤሆሙ እስከ ይገብሩ ዕርቀ ወሰላመ" ይላልና:: ነገር ግን ይህንን ተፈጻሚ ለማድረግ ሰበካ ጉባኤውም ወረዳ ቤተክህነቱም በሀገረ ስብከት ማስጸደቅ ይገባቸዋል:: ቃለ ዐዋዲ 12፥4 ላይ እንደተገለጸው ምሥጢራትንና ሥልጣነ ክህነትን በተመለከተ ሰበካ ጉባኤም ተወያይቶ መወሰን ይችላል:: ውሳኔው ተፈጻሚ የሚሆነው ግን በየደረጃው ላሉ አካላት እስከ ሀገረ ስብከት ታውቆ ሲጸድቅ ነው::

፳፫. "ከአራቱ መንበር ውጭ ሊቃነ ጳጳሳት ሌላ የለም:: የሠራናትን ሕግ ያፈረሰውን ሲኖዶስ ያወግዘዋል" ይላል (ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 4):: ከዚህ አንጻር የእኛ መንበር ከማን ነው?

መልስ፦ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን መንበር መንበረ ማርቆስ ነው::

፳፬. የእስልምና ሃይማኖት ተከታዮች ይገረዛሉ:: እነዚህ ሰዎች ይጸድቃሉ ወይስ ክርስቲያኖች ብቻ ናቸው የሚጸድቁ? ምክንያቱም እስማኤልንም እግዚአብሔር ስለባረከው እንዴት ይታያል?

መልስ፦ በሐዲስ ኪዳን መገዘር ወይም አለመገዘር ከሃይማኖት ጋር የሚያያይዘው ነገር የለም:: ሃይማኖት አንዲት ብቻ ስለሆነች የሚጸድቅ ክርስቲያን የሆነ ብቻ ነው:: ራሱ ክርስቶስ ያላመነ ግን ይፈረድበታል ብሏልና (ማር.16፥16):: እስማኤልን እግዚአብሔር

ባርኮታል። እስማኤል ግን እስላም አይደለም። እስልምና የተመሠረተ በ7ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ነው። እስማኤል ደግሞ የነበረ ከዚያ በፊት ገና በብሉይ ኪዳን ዘመን ነው። የእስማኤል፣ የይስሐቅ፣ የአብርሃም ሃይማኖት አንድ ነው የተለያየ አይደለም። እስማኤል የተባረከም በአብርሃም ሃይማኖት ስለነበረ ነው።

፳፫. ቁደር ማጥመቅ የተጀመረው ከግራኝ በኋላ ነው? ከዚያ በፊትስ አልነበረም?

መልስ፦ መጽሐፈ ቁደር መቼ እንደተዘጋጀ አላውቀውም።

፳፬. ቅዱስ ማርቆስ ወንጌላዊ፣ አትናቴዎስ፣ ቄርሎስ፣ ዲዮስቆሮስ ኢትዮጵያዊ ናቸው ይላሉ አባ ተስፋ ሥላሴ እና አስረስ የኔሰው። ልክ ናቸው?

መልስ፦ በሃይማኖተ አበው ቄርሎስም፣ አትናቴዎስም፣ ዲዮስቆሮስም የእስክንድርያ ሊቃነ ጳጳሳት እንደሆኑ ይናገራል እንጂ የኢትዮጵያ እንደነበሩ አይገልጽም። አለማቀፋዊ የቤተክርስቲያን ታሪካቸውንም ስንመለከት ኢትዮጵያ እንደተወለዱ አይገልጽም። በአንጻሩ ግብጽ እንደተወለዱ የሚገልጹ መዛግብት ብዙ ናቸው። ስለዚህ አባ ተስፋ ሥላሴና አለቃ አስረስ የኔሰው ልክ ናቸው ለማለት የሚያበቃ ምንም ማስረጃ አላገኘሁም።

፳፭. አንድ ሰው ዝንየት ያልሆነ ከመደበኛው የዘር ፈሳሽ የተለየ ከራሱ ቁጥጥር ውጪ በማንኛውም ሰዓት በይበልጥ ሽንት ቤት በሚጠቀምበት ሰዓት ፈሳሽ የሚወጣው ከሆነ ወደ ቤተክርስቲያን ከመቅረብ አንጻር ሥጋ ወደሙን ከመቀበል አንጻር ምን ማድረግ አለበት?

መልስ፦ ዝንየት ከመታው ሆን ብሎም ይሁን፣ ሳይታሰበው በዕለቱ መቁረብ የለበትም። ሳይታጠብም ወደቤተክርስቲያን መግባት የለበትም።

፳፮. አምላካችን መድኃኒታችን የተሰቀለበት መስቀል የእንጨት ነው። ነገር ግን እኛ የብረት የብር የወርቅ እናስራለን ለምን?

መልስ፦ እውነት ነው ጌታ የተሰቀለበት መስቀል የእንጨት መስቀል ነው። ስለዚህ በእንጨት መስቀል መሰቀሉን ለመግለጽ የእንጨት መስቀል እንይዛለን። በመስቀሉ የተቸነከረበት ችንካር የብረት በመሆኑ የብረት መስቀል እንይዛለን። ጌታ ንጹሐ ባሕርይ ነው ብለን ንጹሐ ባሕርይነቱን ለመመስከር የወርቅ መስቀል እንይዛለን። ፍሬ ነገሩ የመስቀል ምልክት መሆኑ እንጂ የተሠራበት ነገር አይደለም። ሰይጣናት እንኳ እንኳን ይህንን መስቀለኛ መንገድ ሲያዩ ይፈራሉ ይሸሻሉ ተብሏልና (ፊልክስዩስ)።

፳፱. እሴብሕ ጸጋኪ ዘዘመነ ጽጌ ላይ "ትመስሊ ታቦተ ወትወልዲ ጽላተ" ይላል። ልጇን በጽላት እርሷን በታቦት መስሏታል። ቢያብራሩልኝ?

መልስ፦ በብሉይ ኪዳን ዐሥሩ ትእዛዛት የተጻፉበት ጽላት የሚቀመጥ ሳጥን በሚመስል ታቦት ነበር። ቃለ እግዚአብሔር ኢየሱስ ክርስቶስም በድንግል ማርያም ማሕፀን ዘጠኝ ወር ከአምስት ቀን ቆይቷልና እርሱ በጽላት እርሷ በታቦት ትመሰላለች። በምሳሌ እርሷን መቅደስ ስንል እርሱን ታቦት፣ እርሷን ታቦት ስንል እርሱን ጽላት፣ እርሷን ጽላት ስንል እርሱን በጽላቱ የተጻፈው ቃል እንለዋለን። እርሱን በጽላት ስንመስል የሚዳሰሰው ጽላት የትስብእት ቃሉ የቃል ምሳሌ እየተባለ ይመሰላል።

፴. በአሁን ጊዜ በአገራችን ላይ የግል ሰብእና (personal development) አንቂ ንግግር (motivational speaking) እየተባለ በየቦታው እየተሰጠ ይገኛል። ማለትም ሥልጣናው highlightly ሲታይ አሪፍ ይመስላል። ሥልጠናዎቹ አንድ ሰው ያለውን ተሰጦኦ እንዲያውቅ፣ ብቃቱን እንዲያሳድግ የኑሮ ጥራቱን እንዲያሻሽል ሕልሞቹን እንዲያሳካ በሚል የሚሰጥ ትምህርት ነው። ሥውር ነገራቸው አብዛኛው ግን (ሥልጣናውቹ ብዙዉን ጊዜ በውስጥህ ያለውን ተጠቀም (the power of divinity) አንተ የማትሸነፍ ነህ የራስህ እድል ፈጣሪ አንተ ነህ እያሉ የሰው ልጅ በራሱ እምነት ብቻ እንዲተማመን የማድረግ ኀይል አላቸው ተብለው ይታሰባል። በአጭሩ አመለካከተህን ስትቀይር ሕይወትህ ይቀየራል። የመሳብ ሕግ (the law of attraction) ያሰብከውን ወደ ራስህ ትስባለህ፤ ሚዲቲሽን (meditation) በምናብ ማየት positive thinking, afarimation, energy, frequency በማስተካክል የምትፈልገውን ነገር ሁሉ ማግኘት ትችላለህ የሚሉ ልምምዶች አሏቸው። ከኦርቶዶክስ አሰተምህሮ ጋር እንዴት ይታያል? አንድ ኦርቶዶክሳዊ ይህን ሥልጠና ቢወስድ ችግር አለ?

መልስ፦ ከላይ የተጠቀሱት ክህሎትን ማዳበር፣ ሕልምን ማሳካት፣ አቅምን አሳውቆ ሰው የተሻለ እንዲሆን ማድረግ መልካም ነገሮች ናቸው። ከታች የተጠቀሱት አንተ የማትሸነፍ ነህ፣ በምናብ/በቅዠት መመሰጥ የሚለውና የመሳሰሉት ደግሞ ውሸቶች ናቸው። ማንኛውም ፍጡር መሸነፍ የሚችል ነው። የማይሸነፍ እግዚአብሔር ብቻ ነው። ስለዚህ በአንተ ገለጻ መሠረት ሥልጠናው መልካም ነገርን ከክፉ ነገር ጋር ቀላቅሎ የሚሰጥ ከሆነ ኦርቶዶክሳዊ ሰው መውሰድ የለበትም። ይህ ሥልጠና ግማሽ ታቦት ግማሽ ጣዖት ነውና። ነገር ግን ኦርቶዶክሳዊ አስተምህሮን የማይሽሩ አቅምን የማጎልበቻ ሥልጠናዎች፣ የክህሎት፣ የዕውቀት ሥልጠናዎችን መሠልጠን ችግር የለውም።

፴፩. በጸሎት ጊዜ ዓይንን መጨፈን ክልክል ነው?

መልስ፦ አዎ በጸሎት ጊዜ ዓይንን ወደሰማይ አቅንቶ መጸለይ እንጂ ዓይንን መጨፈን አይገባም። ጌታም አብነት የሆነን ዓይኑን ወደ ሰማይ አቅንቶ በመጸለይ ነው (ዮሐ.11፥41)።

፴፪. የእኔ ጥያቄ ስለውዳሴ ከንቱ ነው። አንድ ሰው የጀመረውን የትሩፋት ሥራ ሳይፈልግ ሰው ቢያየው ማቋረጥ አለበት ወይስ መቀጠል አለበት?

መልስ፦ መቀጠል አለበት። ከንቱ ውዳሴ የሚባለው ሌሎች ሲያመሰግኑን ምስጋናው ይገባኛል ብሎ በልብ መቀበል እንጂ እንደዚያ መባል በራሱ ከንቱ ውዳሴ አይሆንም። እኛ ምስጋና ለእግዚአብሔር ነው ብለን ካልተቀበልነው ከንቱ ውዳሴ አይሆንብንም። ይገባኛል ብለን አስበን ውስጣችንን ደስ ካሰኘነው ግን ምስጋናን ከአፈር/ከበስባሽ ፍጥረት ፈልገናልና ከንቱ ውዳሴ ይሆንብናል።

፴፫. አንዳንድ መምህራን የካህን ሚስት ከዲያቆን ትበልጣለች ይላሉ። ለዚህም ማስረጃ ብለው የሚናገሩት ታቦት ወድቆ ቢገኝ ካህን በዚያ ባይገኝ ዲያቆንና የካህን ሚስት ቢኖሩ እሷ ናት የምታነሣው ይላሉ። ልክ ናቸው?

መልስ፦ አይደሉም። ታቦት ወድቆ ቢገኝ ክህነት ያለው ይሸውም ቄስና ከዚያ በላይ የሆነ ያነሣዋል እንጂ ዲያቆንም የቄስ ሚስትም ታቦት መንካት አይችሉም። ያዛ ታቦተ ጽዮን እንዳትወድቅ ለመደገፍ በመሞከሩ ተቀስፏል። ሐሳቡ መልካም ቢሆንም ለሥርዓት መገዛት ይበልጣልና። ስለዚህ ከላይ የተገለጸው ሐሳብ መጽሐፋዊ መሠረት የለውም። ከቄስ ሚስትም ዲያቆን ይበልጣል። ዲያቆን ከመዓርገ ካህናት አንዱ ስለሆነ መቅደስ ይገባል ልብሰ ተክህኖ ይለብሳል የቄስ ሚስት ግን ይህንን ማድረግ አትችልም።

፴፬. ኤአይን ከቤተክርስቲያንና ከክርስቲያናዊ ሕይወት አንጻር እንዴት መጠቀም አለብን? በአሁኑ ሰዓት ያለአግባብ ብዙ ቅዱሳት ሥዕላት በAI እየተሠሩ ነው። ኤአይ በጣም ብዙ የቤተክርስቲያን ዕውቀት (ግእዝን ጨምሮ) ባለቤት እየሆነ ነው (ይህም የሚሆነው እኛው ለኤአይ share, chat በምናደርጋቸው ነገሮች የመሆን ዕድሉ ከፍተኛ ነው)። ይህ ለቤተክርስቲያን ደህንነት ስጋት አይሆንም ወይ?

መልስ፦ ቴክኖሎጂውን የፈጠርነው እኛ ስላልሆንን የማጥፋት ሥልጣን የለንም። የቴክኖሎጂውን ጥቅምና ጉዳት አስልቶ መጠቀም ግን እኛ ማድረግ የምንችለው ነው። ቅዱሳት ሥዕላት በማሽን፣ በኮምፒውተር፣ በኤአይ መሳላቸው ተገቢ ነው ወይስ አይደለም የሚለውን እንደዘመኑ ሁኔታ አይቶ ቀኖና የመቀነን ሥልጣን የቅዱስ ሲኖዶስ ነው። መለኪያ መስፈርት ባልተቀመጠበት ሁኔታ ልክ አይደለም ወይም ልክ ነው ማለት አይቻልም። ሚዛን ከሌለ ሁሉም ልክ ነው ሁሉም ልክ አይደለም። ቤተክርስቲያን በራሷ ሥርዓት እስከተመራች ድረስ ምንም ጉዳይ ስጋቷ አይሆንም።

፴፭. አንድ ሰው እግዚአብሔር የፈቀደለት ሕይወት (ትዳር ወይም ምንኩስና) የቱ እንደሆነ የሚያውቅባቸው መንገዶች ምንድን ናቸው? ለትዳር ወይም ምንኩስና የሚደረጉ ቅድመ ዝግጅቶችስ ምንድን ናቸው?

መልስ፦ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለእግዚአብሔር እንተውለት። የእግዚአብሔርን ፈቃድ ሰው ማወቅ አይችልም። ስለዚህ ሰው ለመመንኮስ ከፈለገ ቁርጥ ኀሊና አድርጎ መመንኮስ ነው። ማግባት ከፈለገ ማግባት ነው። ይህ የነጻ ፈቃድ ጉዳይ ነው። በምንኩስናም በትዳርም ያሉትን ፈተናዎች አመዛዝኖ ቁርጥ ኅሊና አድርጎ መምረጥ ነው። ሁለቱንም የሕይወት መስመሮች እግዚአብሔር ፈቅዷል። ከዚህ በኋላ መርጦ መወሰን የእኛ ፈንታ ነው።

፴፮. ስለ ታቦት እና ጠረጴዛ ንገሩኝ?

መልስ፦ ታቦት የሚባለው በሐዲስ ኪዳን የክርስቶስ ሥጋና ደም የሚፈተትበት፣ አልፋ ወኦ ቤጣ የውጣ የሚሉ የእግዚአብሔር ስሞች የተጻፉበት የከበረ ንዋይ ቅዱስ ነው። ጠረጴዛ የሚባለው ደግሞ ታቦቱ የሚቀመጥበት መንበር ነው። ቅዳሴ ያዕቆብ ዘሥሩግ ትርጓሜ ላይ "እንዘ ናነሥእ እደዊነ ዲበ ዛቲ ጠረጴዛ። እደ ልቡናችንን አንሥተን በዚህ በመንበሩ ላይ በምንፈትተው በዚህ አምሳል" ይላልና። በእርግጥ በዚህ አገባብ የሚፈተትበት መንበሩ ሳይሆን ታቦቱ ስለሆነ መንበር ያለው ታቦት መሆኑ ግልጽ ነው።

፴፯. ፍትሐ ነገሥት አንቀፅ 7፥249-250 ላይ "ዲያቆን ያስተምርና ያጠምቅ ዘንድ ወይም ይቀድስ እና ያጠምቅ ዘንድ ሥልጣን የለውም። ዲያቆን ቁርባኑን አይሸከም ኤጵስ ቆጶስ ወይም ቄስ ቁርባኑን በያዘ ጊዜ እርሱ ግን ለሕዝቡ ደሙን ያቀብል። እርሱ የካህናት አገልጋይ እንጂ ካህን አይደለም" ይላል። ዲያቆን ያስተምር ዘንድ ሥልጣን የለውም ሲል ምን ማለት ነው? ዲያቆን ካህን አይደለም ሲል ምን ማለት ነው?

መልስ፦ ዲያቆን ያስተምር ዘንድ ሥልጣን የለውም አይልም። መጽሐፉ የሚለው ያስተምርና ያጠምቅ ዘንድ አይቻለውም ነው። ይኸውም አስተምሮ ማጥመቅ አይችልም ማለት ነው። ማጥመቅ የቀሳውስት፣ የቆሞሳት፣ የኤጲስ ቆጶሳት፣ የጳጳሳት ሥራ ነውና። ዲያቆን የካህናት አገልጋይ እንጂ ካህን አይደለም የሚለው በመዓርግ ከቀሳውስት ያነሠ በመሆኑና ማጥመቅ፣ ማቊረብ ስለማይችል ነው። የአገልግሎቱን ውሱንነት ለማመልከት የተነገረ ነው። ካህን አይደለም ባለ ጊዜ ካህን የሚተረጎም ከማጥመቅ ከማቊረብ ከማሰር ከመፍታት ጋር ተያይዞ ነው።

፴፰. ልጅ እያለን መሪጌቶች የነገሩን እና እነርሱም እንደሚጠቀሙበት ያሳወቁን ጸሎት ነበር። መንገድ ስትሔድ በተለይም ደግሞ ሌሊት ላይ ብቻህን ወደ ፈለከው ቦታ ስትንቀሳቀስ ይህንን ጸሎት ሰባት ጊዜ ደግመህ ከሆነ አጋንንት አርባ ክንድ ይርቅሃል ብለውናል። መሥራትና አለመሥራቱን ባላውቅም እኔም እጠቀምበት ነበር። ባልታወቀ ምክንያት ግቢ ስገባ ነው የተውኩት። ጸሎቱ ይህ ነው "ሳዶር አላዶር ዳናት አዴራ ሮዳስ በአምስቱ ቅንዋተ መስቀል ጸእ

**መንፈሰ ርኩስ ርግብ ጸአዳ ምድር በድንጋጤ ተረዳ አትልፋ በሉት ያን ርኩስ ገዝተውታል አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ" ይላል። ይህን እንዴት ያዩታል?**

መልስ፦ አምስቱን ቅንዋተ መስቀል ጠቅሶ ሰይጣን ሆይ ራቅ ማለት መልካም ጸሎት ነው። ርግብ ጸዓዳ ምድር በድንጋጤ ተረዳ ያለው ያልተሟላ ዓረፍተ ነገር ነው። ርግብ ጸዓዳ የተባለ መንፈስ ቅዱስ ነው ወይስ እመቤታችን? ከሁለቱ አንዱ ቢሆንም ቀጥሎ ያለው ዓረፍተ ነገር "ምድር በድንጋጤ ተረዳ" የሚለው ስሜት አይሰጥም። የሆነ ሆኖ በሃይማኖት ትምህርት ላይ ከልብ ሆኖ የእግዚአብሔር ረድኤት እያሰቡ መጸለይ እንጂ ምሥጢሩ ከቁጥሩ አይደለም።

**፴፱. የዕብራብውያን ትርጓሜ 2፥15 ላይ ጥንቱን ሰው ሲፈጠር በዘር ምክንያት በጽነት አንድ አንዱን እየሰደደ በማሕፀን ይቆራኘው ነበር። ኗላም በዚህ ዓለም ኃጢኣት ሲያሠራው ጣዖት ሲያስመልከው ይኖር ነበር ይላል። በማሕፀን ያለ ሕፃን ምን ዓይነት ጽነት ኖሮት ነው? ቁራኝነት ማለትስ ምን ማለት ነው?**

መልስ፦ ቁራኝነት የሚለው መርገምን ነው። ይህ መርገም ደግሞ በአዳም የባሕርይ ጉስቁልና ምክንያት የመጣ ስለሆነ ሕፃናት በደሉም አልበደሉም የአዳም ልጅ በመሆናቸው ብቻ ያገኛቸው የነበረ መርገም ነው። ይህንን መርገም ክርስቶስ በተፀነሰ ጊዜ ከሰው ልጆች ሁሉ አርቆታል። መርገም የሚባለው መራብ፣ መጠማት፣ መሞት፣ ቁራኝነትና የመሳሰለው ነው። እነዚህ ነገሮች ደግሞ ጽነት ኖረም አልኖረም በሰው ልጆች ሁሉ ሲደርሱ የነበሩ ነገሮች ናቸው።

**፵. ቅድስት ሥላሴ ሲሣሉ ዓለምን በእጃቸው ይዘው ነው። የዓለምን ቅርጽ እንደዚያ አድርገን የምንሥለው ለምንድን ነው? ሌላው ደግሞ ሦስቱ ሥላሴ ማለት ይቻላል?**

መልስ፦ ቅዱሳት ሥዕላት ጥቂት ሁነቶችን ለማስተማርና ለመግለጽ ይጠቅሙናል እንጂ የአንድ እውነት ሙሉ ነገርን የያዙ አይደሉም። ሦስቱም ዓለምን ይዘው መታየታቸው። አኀዜ ዓለም በእራሱ ያለውን ዓለምን የያዙ መሆናቸውን ለመግለጽ የተሣለ ነው። ሦስቱም ተመሳሳይ ገጽ ያላቸው በአካል፣ በመልክ፣ በገጽና በመሳሰለው ተመሳሳይ ስለሆኑ ይህንን ለሰው በሚገባው ለመግለጽ ነው። እንጂ የሥላሴ አካል ወሰን የለበትም። ከሥዕል የረቀቀም ስለሆነ መሣል አይችልም። የዓለም ቅርጽም ለጊዜው ሠዓሊው በዚያ የወከለው ሆኖ ነው እንጂ የዓለምን ቅርጽ የሚያውቁት ራሳቸው ሥላሴ ናቸው። ቅዱሳት ሥዕላት ውክልናዎች እንጂ አማናዊ መልክን፣ ቁመናን የሚያመለክቱ አይደሉምና። ሦስቱ ሥላሴ ግን አይባልም። ሥላሴ ማለት ሦስትነት ማለት ነው። ሦስቱ ሦስትነት ወይም ሦስቱ ሦስቶች አይባልምና። ልዩ ሦስት የሆነ አንድ መለኮት ነው ያለውና።

፵፩. በአሁኑ ዘመን በሕክምናው ዓለም ብዙ ሥራ ይሠራል። አንዱም የጸጉር ንቅለ ተከላ ነው። ይሄ ጉዳይ ከሃይማኖት አንጻር እንዴት ይታያል ማስተከል ይቻላል?

መልስ፦ ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 11 ላይ ኢትወስክ ሕብረ በዲብ ሕብርከ፣ እግዚአብሔር በሰጠህ መልክ ላይ ሌላ መልክ አትጨምር ይላል። ስለዚህ ጸጉር የሌለው ሰው መላጣነቱን አምኖ መኖር እንጂ የሌለውን ጸጉር ማስተከል የለበትም። መላጣነትኮ የሆነ ደስ የሚል ነገር አለው (ማጽናኛ😁)። ሌሎች የንቅለ ተከላ ዓይነቶች ከበሽታ ለመዳን፣ ሌላውን ለማዳን የሚደረጉ እንደ ዓይንን መለገሥና ኩላሊትን መለገሥ፣ ደምን መስጠት የመሳሰሉት ደግሞ ከዘመኑ ሕክምና አንጻር ሲኖዶስ ብያኔ ቢሰጥባቸው ብዬ አልፋለሁ።

፵፪. በፍሬ ቅዳሴ ላይ ካህኑ ንፁሕ የሆነ ከቁርባኑ ይቀበል ብሎ እጁን ከታጠበ በኋላ ውሃውን በእጁ ወደ ቀኝም ወደ ግራም ይረጫል እና ይህ ልማድ ነው ወይስ ሥርዓት ነው?

መልስ፦ ይህ ሥርዓት ነው። ምሥጢሩ ግን ንስሓ ሳትገቡ በድፍረት ብትቆርቡ እኔ ከበደላችሁ ንጹሕ ነኝ ማለት ነው።

፵፫. ስንጸልይ ይህንን አድርግልኝ ብሎ መለመን እግዚአብሔርን እንደአላዋቂ መቁጠር ነው። የልቡናን ያውቃል ሚሉ አባቶች አሉ። ደግሞ ለምኑ ይሰጣችኋል ይላል። ስንለምን በዝርዝር መጸለይ ወይስ የልቡናዬን መልካም መሻት ስጠኝ ማለት?

መልስ፦ እግዚአብሔር አያውቅም ያለ የለም። እግዚአብሔር ራሱ ለምኑ ይሰጣችኋል ብሏልና። የሰው ልጅ ነጻ ፈቃድ አለው። ስለዚህ መሻቱን በጸሎት ማሳወቅ አለበት። እንጂ እግዚአብሔር ያውቃል እኔ አልለምንም ማለት አይገባም። ይህ የሰነፍ አነጋገር ነውና። እግዚአብሔር የልባችሁን ስለማወቅ አትጸልዩ አላለምና። ስለዚህ መልካም የመሰለንን ጉዳይ በዝርዝር ሁሉ ያለህ አንተ ነህና ስጠኝ ብለን መለመን ይገባናል። ከዚያ በኋላ የሚጠቅመንን መስጠት የማይጠቅመንን ማስቀረት የእግዚአብሔር ፈንታ ነው።

፵፬. ጥር 12 የቅዱስ ሚካኤል ጽላት ባለበት ቃና ዘገሊላ ይከበራል። በቃና ዘገሊላ የመልአኩ ተሳትፎ ምንድን ነው?

መልስ፦ ጥር 12 የቅዱስ ሚካኤል ወርኃዊ በዓል ነው። ወርኃዊ በዓሉ ከጌታ ዓመታዊ ክብረ በዓል ጋር በአንድ ላይ ስለዋለ ታቦቱ ከጥምቀተ ባሕሩ አድሮ በዋናነት ቃና ዘገሊላ ይከበራል። ከዚህ የዘለለ በቃና ዘገሊላ መልአኩ ምን አድርጎ እንደነበር የተጻፈ ነገር ስላላገኘሁ አላውቀውም።

፵፭. የሰው ገንዘብ ንብረት በግፍ የቀማ በግፍ ለካደ የእግዚአብሔር ፍርድ እንዴት ነው? እኔም በጸሎት ጊዜ አምላኬ ፍረደኝ ብዬ ማልቀሴ ከቂም ይቆጠራል ወይ?

መልስ፦ እግዚአብሔር በባሕርዩ በትክክል የሚፈርድ አምላክ ነው፡፡ ስለዚህ ማንኛውም ሰው ለበደለው በደል ፍርድ አለበት፡፡ ፍርዱ በምን መልኩ እንደሚፈጸም፣ መቼ እንደሚፈጸም፣ እንዴት እንደሚፈጸም የሚያውቀው ግን እግዚአብሔር ብቻ ነው፡፡ በእኛ ላይ ሰዎች ክፉ ቢያደርጉብንም ለሰዎች ክፉ መመኘት የለብንም፡፡ እኛንም እግዚአብሔር ምሮን እንጂ ከልጅነታችን ጀምረን ራሳችንን ብንመረምረው ብዙ ጥፋት ሊገኝብን ይችላልና፡፡ ስለዚህ ለደረሰብን በደል ፍትሕን ስጠን ብለን ፍትሕን መለመን እንችላለን፡፡ እገሌን እንዲህ አድርግልኝ ብለን መጸለይ ግን የለብንም፡፡

፵፮. የማኅበር ጸሎት በመኖሪያ ቤት ውስጥ መጸለይ አይቻልም በቤተክርስቲያን እንጂ የሚሉ አሉ፡፡ እንዴት ያዩታል?

መልስ፦ የቅዳሴ ጸሎትም፣ የማኅሌት ጸሎትም፣ የሰዓታት ጸሎትም የማኅበር ጸሎት ስለሆነ ቅዳሴን፣ ሰዓታትን፣ ማሕሌትን በቤት መፈጸም አይገባም ለማለት ፈልገው ይሆናል እንጂ ከዚህ ውጭ የሆነ ጸሎት በየቤት መጸለይ ይችላል፡፡

፵፯. ለጥምቀት ታቦት ወጥቶ በማግስቱ ሲገባ ሕንጻ ቤተ ክርስቲያን በሩ ላይ በግ ይታረዳል፡፡ ይህ ከቤተክርስቲያን ሥርዓት አንጻር እንዴት ይታያል?

መልስ፦ ይህ ከቤተክርስቲያን ሥርዓት ጋር የሚያገናኘው ምንም ነገር የለም፡፡ እንዲያውም እንዲህ ያለ ነገር ማድረግ አይገባም፡፡ በግ አርደን መብላት ከፈለግን ለብቻው ከውጭ አርደን መብላት እንጂ የበግ እርድን ከሥርዓተ ታቦት ጋር ማገናኘት አይገባም፡፡

፵፰. አንድ ሕፃን ከተጠመቀ በኋላ በውኃው ለልጁ ቤተሰቦች /ክርስትና አንሺዎች/ ሲረጭባቸው ይታያል፡፡ እና ቤተሰቡም ውኃውን በሆነ እቃ አድርገው ይወስዱታል፡፡ ይህ መደረግ ይችላል?

መልስ፦ ሕፃኑ የተጠመቀበት ውሃ ማየ ገቦ ስለሆነ በዚያ ማንም ሊረጭበት አይገባም፡፡ ያንን ቅዱስ ውሃም ማንም ወደቤቱ መውሰድ የለበትም፡፡

፵፱. መቅድመ ተአምረ ማርያም ላይ በሥዕሏም ፊት ስገዱ የሚለው በበዓላት ጊዜ ለምሳሌ እሑድ ምን ዓይነት ስግደት ነው የሚሰገደው?

መልስ፦ ስግደት በምክንያተ ስግደት መሠረትነት ሦስት ዓይነት ነው፡፡ አንደኛው የአምልኮ ስግደት ነው፡፡ ሁለተኛው የቀኖና ስግደት ነው፡፡ ሦስተኛው የአክብሮ ስግደት ነው፡፡ የቀኖና ስግደት ሰው ቀኖና ተሰጥቶት የሚሰግደው ወይንም ደግሞ ትሩፋት ይሆነው ዘንድ ሥጋውን ለማስገዛት የሚሰግደው ስግደት ነው፡፡ ለእግዚአብሔር የምናቀርበው የአምልኮ ስግደት ጸሎት ስንጀምርና ስንፈጽም የምንሰግደው ስግደት፣ ወደ ቤተ መቅደስ ወደ ቤተክርስቲያን ስንገባ የምንሰግደው ስግደት በማናቸውም ጊዜ

ይሰገዳል። በአስተብርኮም በወዲቅም በአድንኖም ቢፈጸም ይሆናል። በቅዱሳት ሥዕላት ፊት ለአክብሮ የምንሰግደውም ስግደት በማናቸውም ጊዜ የምናደርገው ነው። የቀኖና ስግደት ግን በበዓላት አይሰገድም።

፶. 18 ዓመት ሳልሞላ ክርስቲያን ተዝካር ይደረጋል ወይስ አይደረግም? የዕድሜ ገደብስ አለው?

መልስ፦ ተዝካር ማለት ሰውየው ይማር ዘንድ የሚፈጸም የፍትሐት፣ የጸሎት፣ የምስጋና መርሐ ግብር ነው። ማንኛውም ሰው ቢሞት ደግሞ ፍትሐት ይደረግለታል። ስለዚህ ለተዝካር የዕድሜ ገደብ የለውም።

፶፩. ባልና ሚስትን በሚመለከት በጾም ወቅት በስሜታቸው ተሸንፈው የሚያደርጉት ሩካቤ ኃጢአት ሊባል ይችላል? ንስሓስ  መግባት አለባቸው?

መልስ፦ በሰሙነ ሕማማት እና በዓርብ ረቡዕ የሚያደርጉት ግንኙነት ኃጢአት ስለሆነ ንስሓ ይገባበታል። በሌሎቹ አጽዋማት ግን ፍትወት ቢነሣባቸው ከቀኑ ዘጠኝ ሰዓት እስከ ምሽቱ 3፡00 ሰዓት ባሉት ስድስት ሰዓታት ፈቃዱን መፈጸም እንደሚችል ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 24 ትርጓሜ ላይ ተገልጿል። ስለዚህ በሌሎች አጽዋማት ግንኙነት ቢፈጽሙ ትሩፋታቸው ይቀርባቸዋል ከኃጢአት ግን የሚቆጠረው ከላይ የገለጽኩት ነው።

፶፪. ቤተክርስቲያን በዕለተ ዓርብ ከጌታችን ጎን ተገኘች ሲባል ከዚያ በፊት አልነበረችም ማለት ነው? የትኛዋን ቤተክርስቲያን ነው?

መልስ፦ ቤተክርስቲያን ሦስት ትርጉም አለው። የሕንፃ ቤተክርስቲያን መጠሪያ፣ የእያንዳንዱ ምእመን መጠሪያ፣ የሕብረተ ምእመናን መጠሪያ ይሆናል። ቤተክርስቲያን ማለት የክርስቶስ ወገን ማለት ነው። ይኸውም በእግዚአብሔር ክርስቶስ አምነው የሚኖሩ ሁሉ መጠሪያ ይሆናል። በዚህ አግባብ ከሔድን ቅዱሳን መላእክትም በአምልኮተ እግዚአብሔር ጸንተው ስለኖሩ ቤተክርስቲያን ከስቅለት በፊትም ነበረች ብንል ያስኬዳል። ሕንጻ ቤተክርስቲያንን ከሆነ ደግሞ ከስቅለት በኋላ ነው። ቤተክርስቲያን በዕለተ ዓርብ ከጌታችን ጎን ተገኘች ከተባለ ምእመናን የክርስቶስ ወገኖች የሚሆኑበት ማየ ገቦ ከክርስቶስ ጎን ተገኘ ብሎ መተርጎም ነው።

፶፫. ማንኛውም ምእመን በመኖሪያ ቤቱ እና በጸሎት ቤቱ ዕጣን ማጠን ይችላል?

መልስ፦ ከቤተክርስቲያን የገባ ዕጣንን ወደቤቱ ወስዶ ማንም ያጥን ዘንድ አልተፈቀደለትም። ቤተክርስቲያን ሳይገባ ከገበያ ገዝተን፣ ወይም ከዱር ለቅመን አምጥተን ከሆነ ግን አልተከለከለም። ይህ ዘቢብንም ይመለከታል። ወደ ቤተክርስቲያን

ከገባ ማንም ወደቤቱ አምጥቶ መጠቀም አይችልም። ከውጭ ከሜዳ አግኝቶ ከገበያ ገዝቶ ግን ፍሬውን ሊበላ፣ ከዚያም በፊት ወይን ጨምቆ ሊጠጣ ይችላል።

፶፬. ስለ ቅዱሳት ገድላት እና ድርሳናት እንዲህ ብለው ጠየቁኝ ማን ነው የደረሳቸው ለምሳሌ ድርሳነ ሚካኤል ላይ ቅዱስ ሚካኤል መጥቶ ሲያናግራቸው ሲረዳቸው ሁሉ ድርሳኑ ላይ አለ። ከገድላትም እንደዚሁ መላእክት መጥተው ሰማዕታትን ሲያጽናኗቸው እንዲሁም ራሱ እግዚአብሔር እንደሚያጽናናቸው አለ። ይህ ሀሉ ሲደረግ ደራሲው እንዴት ነው አብሮ እየሰማ ነበር? አንድ መንፈሳዊ ድርሰት የቤተክርስቲያን የሚባለው ምንን ሲያሟላ ነው?

መልስ፦ የገድላትና የደራስያን ጸሓፊዎች እግዚአብሔር ገልጾላቸው ደጋግ ሰዎች ናቸው። ስለዚህ የመላእክትን ተራዳኢነት፣ የቅዱሳኑን ቅድስናና ያደረጉትን ተአምር ገልጾላቸው ጽፈዋል። እነዚህ ደጋግ ሰዎች አንዳንዶች በዘመናቸው የነበሩ ወይም ረድኤቱን ያዩ፣ አንዳንዶች በኋላ ዘመን ተነሥተው ተገልጾላቸው ጽፈዋል። አንድ ድርሰት የቤተክርስቲያን የሚባለው ኦርቶዶክሳዊ አስተምህሮን ይዞ ሲገኝ ነው።

፶፭. ዝክር በምንዘክርበት ጊዜ የሰማዕታት፣ የመላእክት ወይም የቅዱሳን ሲሆን ዝክራችንን ዝክረ አብ ዝክረ ወልድ ዝክረ መንፈስ ቅዱስ ያድርግልን እንላለን። የራሱ የመድኃኔዓለም ሲሆን ዝክረ አብ ዝክረ ወልድ ዝክረ መንፈስ ቅዱስ ያድርግልን እንላለን?

መልስ፦ ዝክራችንን ዝክረ አብ፣ ዝክረ ወልድ፣ ዝክረ መንፈስ ቅዱስ ያድርግልን የሚለው ጸሎት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያንን የነገረ ቅዱሳን ትምህርት አጉልቶ የሚያሳይ ነው። በቅዱሳን መታሰቢያ ዝክር እንኳ በዋናነት የሚታሰበው፣ የሚዘከረው፣ የሚመሰገነው ራሱ እግዚአብሔር ለመሆኑ ገቢራዊ ትምህርት ነው። በመድኃኔዓለም ዝክርም የሚታሰብ ራሱ ስለሆነ ይህንኑ ቃል ቢሉት ምንም ችግር የለውም። አዎ እንላለን።

፶፮. ቁደር የሚደገም ሥርዓት ነው ወይስ አይደገምም?

መልስ፦ ቁደር እንደየሁኔታው ሊደገም ይችላል። ቁደር የንስሓ ጥምቀት ነው። ምሥጢረ ንስሓ ደግሞ በድለን ከተገኘን ሊደገም የሚችል ነውና።

፶፯. ከሌላ እምነት ሰዎች ጋር ጸሎት ማድረግ አግባብ ነውን?

መልስ፦ አይደለም። ከሌላ እምነት ሰዎች ጋር ተዳድሎ (በል አንተ ቀጥዬ እኔ ልበል እየተባባሉ) በቦታ በአንድ ላይ ሆኖ መጸለይ አይገባም። ከተወገዙ ሰዎች፣ ከሌላ እምነት ሰዎች ጋር አትጸልይ ተብሎ ተጽፏልና (ሃይ.አበ.21፥42)።

፶፰. አንድ ዲያቆን አለ የሚወዳት ፍቅረኛው ውጪ ሀገር ናት፡፡ በ13 ዓመቷ ስትወጣ በባሕር ስለነበር መንገድ ላይ ተደፈረች፡፡ እና እርሱ በጣም ይወዳታል እርሷም በጣም ትወደዋለች፡፡ ሁለቱም ይዋደዳሉ፡፡ በተክሊል መጋባት ይችላሉ?

መልስ፦ ዲያቆን እርሱም ድንግል ሆኖ የሚያገባትም ድንግል ሆና ነው የሚጋቡት፡፡ ምንም እንኳ በግድ የተደፈረች ቢሆንም ዙሮ ዙሮ ድንግልናዋን አጥታለች፡፡ ስለዚህ በተክሊል ማግባት አትችልም፡፡ ምናልባት አስተያየት የሚደረግበት ሁኔታ ካለ ግን ይህ ቀኖና ስለሆነ የሚመለከታቸውን አካላት ለምሳሌ የሀገረ ስብከቱን ሊቀ ጳጳስ ማማከር ብትችል መልካም ነው፡፡ የእኔ መልስ ግን መጀመሪያ ላይ የተናገርኩት ነው፡፡

፶፱. አንድ ካህን በተለያየ ምክንያት ከሚስቱ ቢጣላ ወይም ብትሞትበት ሌላ ሴት አግብቶ መስቀል ማሳለም ይችላል?

መልስ፦ አይችልም፡፡ ሚስቱ ሞታበት ሳያገባ በዚያው በንጽሕና ከኖረ እያሳለመ እየቀደሰ መኖር ይችላል፡፡ ሌላ ካገባ ግን ክህነቱ ስለሚፈርስ መስቀል ማሳለምም ሌሎች የክህነት ሥራዎችንም መሥራት አይችልም፡፡

፷. የስምንት ወር እርጉዝ የሆነች ሴት ቅዱስ ቁርባን መቀበል ትችላለች?

መልስ፦ አዎ ትችላለች፡፡ ምናልባት ለመውለድ ቀኗ ከመድረሱ የተነሣ የሚያጋጥማት ፈሳሽ ነገር ወይም ሌላ ነገር ከሌለና ለመቁረብ የሚያስፈልጉ ዝግጅቶችን ማድረግ ከቻለች መቁረብ ትችላለች፡፡

፷፩. የምወዳትን ጓደኛዬን እግዚአብሔር ወስዶብኝ በኀዘን መጽናናት አልቻልኩም፡፡ በእኔም ደርሶ ከዚህ በፊትም በሰዎች ሲደርስ እነዚህ ጥያቄዎች አሉኝ፡፡ የሊቅ ሊቅ የሆነ መልስ ነው የምፈልገው፡፡ ሌላውን እኔም አውቃለሁ፡፡ በተለይ እግዚአብሔር ሥራው አይመረመርም፡፡ "እዚህ ብትቆይ ትቆሸሽ ይሆናል አስቀድሞ የወሰዳት ለእርሷ ከዚያ ይሻላታል ወዘተ" የሚለው መልስ አይሆነኝም፡፡ ለምን የ19 ዓመት ምስኪን ልጅ ገና ሕይወትን ማየት የናፈቃት ድንገት ታማ በሕክምና እርዳታ ማነስ ይሁን፣ በምን ይሁን ባላውቅም የሚሳሱላት በተለይ እናት እያለች ለምን እግዚአብሔር በሞት ይወስዳታል? እናት ቁጭ ብላ በልጇ ሞት እርር እንድትል ለምን ይፈቅዳል? ቤተሰብ በኀዘን እንዲቃጠል ለምን ይፈቅዳል? መቼም አያስደስተውም ይኼ የሚያስደስተው ሰይጣን ነው፡፡ ስለዚህ አጋንንት ሠልጥነው ሕይወት የሚነጥቁ ከሆነ ደግሞ (ማለትም በመተት፣ በሚበላ በሚጠጣ ነገር ሰው ክፉ ነገር አድርጎም ቢሆን) እናትንና ወዳጆቿን በኀዘን ማሰቃየት ማስለቀስ ማሳረር ያስደስተዋል፡፡ ሰይጣን ካደረገው ደግሞ ለምን እግዚአብሔር ፈቀደለት ለምንስ ዝም ይላል? በዚህ የሚሰቃየው አብዛኛው ደግሞ እግዚአብሔርን በማምለክ ታግሦ ሕይወቱን በመጠነኛ ኑሮ የሚገፉ ድኻና የድኻ ልጅ ነው፡፡ ለምን? እሺ በሞት ከወሰዳት እናቷን ቤተሰቧን ለምን በቶሎ አያጽናናም? ለምን በቶሎ

ልባቸውን ድንጋይ አያደርገውም? አንድ ልጃቸውን እምቦቃቅላ ወስዶ ለምን እርር ድብን ቅጥል ሲሉ ዝም ይላል።

መልስ፦ በእውነቱ ይህ ጥያቄ አስጨናቂ ነው። ልመልሰው አስብና ጠያቂው ግን የሊቅ ሊቅ የሆነ መልስ ነው የምፈልገው በማለታቸው እኔ ደግሞ የሊቅ ሊቅ ስላልሆንኩ ልተወው አሰብኩ። እንደገና ጉዳዩን ዝም እንዳልለው አንዳንድ ነገሮች ላይ ተናገር ተናገር አሰኘኝ። ገጣባ አህያ ሲጭኗት እንደምትቁነጠነጠው ያለ ነው። ስለዚህ ክቡር ጠያቂ ሆይ እርስዎ የጠበቁትን የሊቅ ሊቅ የሆነ መልስ ማቅረብ ባልችልም የሊቅ ተማሪ እንደመሆኔ የሊቅ ተማሪ መልስ የአቅሜን ልሞክር። በመሠረቱ ኀዘን በጣም ከባድ ስለሆነ ያዘነን ሰው ሐሳብ ማጣጣል አይገባም። ኀዘኑ እስኪያልፍ ብንችል ማጽናናት ባንችል ደግሞ ዝም ማለት የተገባ ነው። የኀዘንን ጽናት ለመግለጽ የዜማ መምህራን የዜማ ምልክት እስከማድረግ ደርሰዋል። "ኀዘን ልቤን ሰበረው፣ በምን ክንፌ ልብረረው" ብለው የኀዘንን አስከፊነት ገልጸውታል። የሆነ ሆኖ ስለተፈጥሯችን አንዳንድ ነገሮችን ማለት ፈልግሁ። እኛ ሰዎች ውሱንነት አለብን። ይህንንም ስንል የዕድሜ ወሰን፣ የዕውቀት ወሰን፣ የአካል ወሰንና የመሳሰሉት አሉብን ማለቴ ነው። ለምን አካል ውሱን ሆነ ስንል ተፈጥሯችን ስለሆነ ነው። የሰው ልጅ ወደዚህ ምድር የመጣው አስቦ፣ አስልቶ በዚህ ጊዜ ልወለድ ብሎ አይደለም። መፀነሱ፣ መወለዱ፣ ማደጉ፣ መሞቱ በእግዚአብሔር ቸርነት የሚሆን ነው። በጠቅላላው የሕይወት ፍልስፍናን ወሰን መረዳት አለብን። የማንኛውም ሰው መፀነስ፣ መወለድ፣ ማደግ፣ መሞት ከእኛ ውጭ በሆነ ኀይል (እግዚአብሔር) የሚከናወን ነገር ነው። እግዚአብሔር እኒህን ነገሮች ለምን፣ መቼ፣ እንዴት እንደሚያደርጋቸው የሚያውቅም እርሱ ራሱ ነው። እኛ ስለእርሱ አስተያየት ለመስጠት አቅሙ የለንም። ይህቺ ምድር ኀላፊ መሆኗን ነግሮናል። በዚህ ምድር የሚገጥመን ኀዘን በኋለኛው ዘመን ኃጥኣን ብንሆን የሚደርስብንን ኀዘን እንድንረዳበትና ከዚያ ፍጹም ኀዘን ካለበት ቦታ እንዳንገባ የኀዘንን ምሬት ተረድተን በዚህ ዓለም ደግ ሕይወትን እንድናሳልፍ ነው። በሌላ መልኩ ይህች ዓለም ኀዘን የበዛባት መሆኗን ተረድተን ከዚህች ዓለም የተሻለች ኀዘን የሌለባትንና ፍጹም ደስታ ያለባትን መንግሥተ ሰማያትን ተስፋ አድርገን እንድንኖር ነው። ከጠያቂያችን አጠያየቅ የተረዳሁት ወይም የመሰለኝ ነገር ግን ሥጋዊ ሞትን የጉዳት መገለጫ አድርገው ማቅረባቸው ነው። የሚወዷት ልጅ በ19 ዓመቷ አርፋለች። በዚህም ጽኑ ኀዘን እንደደረሰባቸው ከጽሑፋቸው መረዳት ይቻላል። በሥጋ መሞት ግን ለደጋግ ሰዎች ዕረፍት ነው። ሲጀምር በዚህ ዓለም የምንኖረው አንድ ቀን ለመሞት ነው። ፍሬ ነገሩ ሞት አይደለም። መሞታችን አይቀርማ። የሁሉንም ሟቾች ታሪክ ብናጠና በእነርሱ ሞት በጣም ያዘነ ሰው ይኖራል። ትልቁ ቁም ነገር ኖረን ኖረን ዙሮ ዙሮ መሞታችን ካልቀረ የመኖር ጥቅሙ ምንድን ነው የሚለውን መረዳት ነው። የመኖር ጥቅሙ በዚህ ምድር ሳለን ለወዲያኛው የደስታ ዓለም የሚያበቃንን ሥራ ለመሥራት ነው። ሁሉም

ሰው ፈጣሪ እንዲኖር ያሰበለትን ጊዜ ሲጨርስ ይሞታል። ይህ የእግዚአብሔር ሥራ ነው። ይህ በእኛ ቁጥጥር ያለ ነገር አይደለም። ስለዚህ የእግዚአብሔርን ሥራ ለእግዚአብሔር ሰጥተን ራሳችን ማድረግ ከምንችለው ላይ ማተኮር ይገባል። የዓለምን ታሪክ ስናጠናው ከመጀመሪያዎቹ ሰዎች ጀምሮ ኀዘን አለ። አዳምና ሔዋን የሚወዱትን አቤል በሞት ተነጥቀዋል። ኦርዮ በግፍ ተገድሏል። ራሔል የወለደቻቸውን ልጆች ከጭቃ ጋር እንድትረግጣቸው ታዝዛለች። እስጢፋኖስ የመዳንን ትምህርት ቢያስተምር በሕዝቡ በድንጋይ ተደብድቦ ሞተ። ሕፃኑ ቂርቆስ ወደፈላ ውሃ ተጣለ፣ በመጋዝ ተተረተረ። ሰማዕታት አሳዛኝ በሆነ አገዳደል ተገደሉ። ይህ ሁሉ ቢሆንም ፈጣሪያቸው ከሞት በኋላ ሰማያዊ አክሊልን አቀዳጅቷቸዋል። የሚወዱትን በሞት በማጣት ምክንያት ማዘን የጤናማ ሰው ምልክት ነው። ነገር ግን ትንሣኤ መኖሩን አምኖ እግዚአብሔር የሚያደርገው ነገር ሁሉ በእኛ ውሱንነት ምክንያት መረዳት ባንችልም ለሚቱም ለነዋሪዎቹም ለበጎ እንደሆነ መረዳት አስፈላጊ ነው። በነገራችን ላይ ሰይጣንም ቢሆን በደጋግ ሰዎች ሞት በጣም ነው የሚያዝን። ምክንያቱም ነፍሳቸውን አጥቶታልና። ሰይጣን የሚደሰት በክፉ ሰዎች ሞት ነው። ነፍሳቸውን ማርኳልና። በዚህ ዓለም የሚያጋጥመን ኀዘን ጥቂትና ኀላፊ ስለሆነ፣ ምናልባት የደረሰብንን መከራና ኀዘን ደግሞ እግዚአብሔርን ባለማማረር አንተ ታውቃለህ ብለን ወደ መደበኛ ሥራችን ብንመለስ ዐስበ ትዕግሥትን እናገኛለን። በዚህች በኀላፊዋ ዓለም ደስተኛ ሆነን ኖረን ዘለዓለማዊዋን ሕይወት ከምናጣ በዚህ ዓለም ኀዘንተኛ ሆነን ዘለዓለማዊዋን ሕይወት ብናገኝ ይሻለናል። የዚህች ዓለም ኑሮ ደግሞ ኀዘንና ደስታ፣ መከራና ተድላ፣ ቀንና ጨለማ፣ ድህነትና ሀብት የሚፈራረቁባት መሆኗን ተረድተን በዚህ ዓለም ሳለን ማድረግ ያለብንን አድርገን ማለፍ ይገባናል እንጂ በደስታውም በጣም መደሰት፣ በኀዘኑም በጣም ማዘን አይገባንም። መዝሙረኛው ዳዊት "ሁልጊዜ በእግዚአብሔር ደስ ይበላችሁ" ያለው በሌላው ብንደሰት ስናጣው መሪር ኀዘን እንዳይገጥመን ነው። እግዚአብሔር ግን የማይታጣ ዘለዓለማዊ ስለሆነ ሁሉን አንተ ታውቃለህ ብለን በእርሱ ታምነን እንኑር እላለሁ።

፳፪. ከቅርብ ዐሥርት ዓመታት በፊት ሰው በልጅነት፣ በወጣትነት አይሞትም ሽምግሎ ነው የሚጠራው። አንዳንድ እንደ ጃፓን ያሉ ሀገራት አሁንም ብዙ ሽማግሌዎች አሉ ወጣት አይሞትም። ኢትዮጵያ እና አፍሪካ ግን ሕፃን፣ ወጣት በበሽታ፣ ጥሩ ሕክምና በማጣት ያልቃል። የምንበላው፣ የምንጠጣው ነገር ሁሉ ንጹሕ አይደለም። ከእርሻው ከማሳው እስከ ፋብሪካው ጎጂ ኬሚካል ለደዌ የሚዳርግ ሆኗል። ሀብታሞች በገንዘባቸው ደኅና ነገር መርጠው ይበላሉ። ቢታመሙም ከሀገር እስከ ውጭ ወስደው ያሳክማሉ። ድኻው እና መካከለኛው ግን መሬቱን፣ ያለውን ነገር ሁሉ ጨርሶ ለምኖ ለማሳከም ይጥራል። አንዳንዱ አቅም አጥቶ ባለችው የመንግሥት ሆስፒታል ያሳክማል። የሚታመመውም ድኻው፣ ታሞ ጥሩ ሕክምና ማድረግ የማይችለውም ድኻው፣ ያለችውን ጨርሶ የታማሚው ሕይወት ያልፍና በሐዘን የሚንገበገው ድኻው ነው። ለምን ለድኻው እግዚአብሔር ዕድሜና ጤና ይነፍገዋል?

መልስ፦ ውድ ጠያቂ ይህ ጥያቄዎት እንኳ በጥልቅ ጥናት ያልተመሠረተ፣ ከራስዎ እይታና ልምድ አንጻር ብቻ የደመደሙ ይመስለኛል። ከጥያቄዎት መጀመሪያ ላይ ከዐሥር ዓመት በፊት ሰው በወጣትነት፣ በልጅነት አይሞትም ያሉት ትክክል አይደለም። ከዚያም በፊት የሰው ልጅ በተለያዩ ዘመናት ይሞታል። እንዲያውም ይህንን ያስተዋለ የመነኰሳት ኮከብ አባ እንጦንስ በአንድ ወቅት እንዲህ ብሎ ጠይቆ ነበር። "ጌታ ሆይ አንዳንዱ በሕፃንነቱ፣ አንዳንዱ በወጣትነቱ፣ አንዳንዱ ሽምግሎ ለምን ይሞታል" ብሎ ነበር። እግዚአብሔር ግን ሲመልስለት "እንጦንስ እንጦስ የእግዚአብሔርን ሥራ ልመርምር አትበል" ተብሏል። በእርግጥ የእግዚአብሔርን ሥራ በሰው መገምገም አይቻልም። ሰው ሌላ፣ እግዚአብሔር ሌላ ነውና። ለምሳሌ ሥጋ ይጣፍጣል ወይስ አይጣፍጥም የሚለውን ጥያቄ ለእንስሳትና ለአራዊት ብንጠይቃቸው ተመሳሳይ መልስ አናገኝም። አንዱን ለይተን ትክክል ይህኛው ነው ማለትም አንችልም። የእንስሳት መሥፈርት ከአራዊት መሥፈርት ይለያልና። ስለዚህ አንዳንድ እይታዎች በእግዚአብሔር ሲታዩና በሰውኛ ሲታዩ የተለያዩ ይሆናሉ። በሰውኛ እይታ የእግዚአብሔርን ፍርድ እንመርምር ካልን ግን ውጤቱ የእግዚአብሔር ሳይሆን የሰው ስሜት የተጫነው ይሆናል። ስለዚህ የእግዚአብሔርን ፍርድ ስለማናውቀው የእርሱን ለእርሱ እንተውለት። የሰው ልጅ የሞት ምክንያት ቢለያይም መሞቱ ግን አይቀርም። አንዳንዱ ታሞ ይሞታል፣ አንዳንዱ ከገደል ወድቆ ይሞታል፣ አንዳንዱ እባብ ነድፎት ይሞታል፣ አንዳንዱ በመብረቅ ተመትቶ ይሞታል፣ አንዳንዱ መኪና ተገልብጦ አውሮፕላን ወድቆ ይሞታል። ድኻውም ሀብታሙም ይሞታሉ። አንዳንዱ ሠርቶ የሠራው ነገር ሁሉ ወይ በተፈጥሯዊ ችግር ወይም በሰው ሠራሽ ችግር ይጠፋበታል። አንዳንዱ ብዙ ሳይደክም ብዙ ሀብት ያገኛል። እነዚህ ሁሉ ሥጋዊ ነገሮች ናቸው። እነዚህ ነገሮች ሁሉ ኀላፊ ናቸው። እኛ ከእኛ የሚጠበቀውን እየሠራን እንኑር። ባለንና በተሰጠን ነገር እግዚአብሔርን ደስ አሰኝተን ለማለፍ እንጣር። የሌላውን ሰው ሁኔታ ለሌሎች ሰዎች እንተውላቸው። እኛ ከድኽነት ለመላቀቅ ጠንክረን እንሥራ። ድኽነት ራሱ ብዙ ዓይነት ነው። ከስንፍና የሚመነጭ ድኽነት አለ። ብዙ ብናገኝ ነፍሳችንን ልናጣ ስለምንችል ለእኛ ዘለዓለማዊ ሕይወት የተሻለ እንዲሆንልን ብዙ ሠርተን እግዚአብሔር በልዩ ልዩ ምክንያቶች እንዳናገኝ ሊያደርገን የሚችልበት ሁኔታም አለ። በየትኛውም መልኩ ቢሆን ግን ባለን እያመሰገንን፣ የፈለግነውን ለማድረግ እየጣርን መኖር ይገባናል። ማንኛውም ኀዘን ቢደርስብን ይህች ዓለም የኀዘን ቦታ መሆኗን ተረድተን ወደፊት መራመድ እንጂ ባለፈው ነገር እየቆዘምን መኖር የለብንም።

፳፫. ሁለት እጮኛሞች ትዳር ሊመሠርቱ የሆነ ቀን ሲቀረው አንደኛው ይሞታል ወይም ትዳር መሥርተው በቀናት ወይም ልጅ ወልደው ወይ አባት ወይ እናት በሞት ይወሰዳል። እናት ስትወልድ ልጅ ይተርፍና እናትየው በሕክምና ትሞታለች ወይም አባት ይሞትና እናት ልጅ ታቅፋ መከራ ልመና ለምን? ሌላው ደግሞ ራሳቸውን ያልቻሉ ልጆችን ጥለው ወላጅ ይሞታል

ልጆች ሜዳ ላይ ይበተናሉ። ታላቅ ለታናናሾቹ ሲል አንዴ አረብ አገር ወይም ግርድና ወይም ያልሆነ ሥራ ወይም ልመና ይገባሉ። አንዳንድ ደግሞ ልጅ ይሰጣቸውና አሳድገው በዓመቱ ወይ በሆነ ጊዜ እየጓጉ፣ ስመው ሳይጠግቡ ይወስዳል። አንዳንዱን ደግሞ ልጄ ደረሰችልኝ ለትዳር፣ ለቁምነገር ብለው እያሰቡ። ወይ ደግሞ ትምህርት ጨርሶ ሊመረቅ ሲል ልጅ ይሞታል። ለምን ይሄ ሁሉ ነገር ያደርጋል ወይም ይህንን የሚያደርግ ሰይጣን ከሆነ ለምን ዝም ይለዋል? ድሮ እኮ እንዲህ ነገር የለም። ወላጅ የሚሞተው ልጆች አድገው ትዳር መሥርተው ነው። ከዚያ እናት ብትሞት መጽናኛ ልጆችና ሚስት አሉት ወይም ልጅና ባል አላት ትጽናናለች። ልጅ ቢሞት እንኳ (ብዙም የለም) ብዙ ልጆች ስላሉ ወላጅ ይጽናናል። ባል ቢሞት ሚስት ልጆች የልጅ ልጆች መጽናኛ ሰጥቷት ነው። ተፈጥሮ ሞት ስለማይቀር ምንም ጥያቄ አይፈጥርም ኀዘኑም ትንሽ ነው። አሁን ግን ተገላቢጦሽ ነው።

መልስ፦ ከዚህ ላይም ጠያቂ የቀድሞውን ታሪክ በእርስዎ መረዳት ላይ ብቻ ተመርኩዘው ወደ ድምዳሜ ሄደዋል። በእርግጥ ጉዳይዎትን ስመረምረው ድሮ የማይደረግ አሁን ለምን ይደረጋል የሚል ሳይሆን በመሠረታዊነት ብዙ የሚያሳዝኑ ነገሮች ሲደረጉ እግዚአብሔር ለምን ዝም ይላል? የሚለው ነው። ከላይ ባሉ ጥያቄዎች ለመግለጽ እንደሞከርኩት እነዚህ ነገሮች ሲደረጉ ዝም ያለበትን ምክንያት የሚያውቀው ራሱ እግዚአብሔር ነው። እኔ በዚህ ምክንያት ነው ብዬ እግዚአብሔርን ወክዬ መናገር አልችልም። ልናገር የምችለው በቅዱሳት መጻሕፍት ይህንን የመሰሉ ድርጊቶች ሲደረጉ የእግዚአብሔር ቃል ምን ነበር የሚለውን ብቻ ልናገር እችላለሁ። የሚደርስብንን ነገር እንደ ኢዮብ እግዚአብሔር ሰጠ እግዚአብሔር ነሣ ማለትን መልመድ አለብን። ጠያቂያችን ብዙ አሳዛኝ ድርጊቶችን ጠቅሰዋል። ሁሉንም ሰው ጥቀሱ ብንል ብዙ አሳዛኝ ድርጊቶችን መጥቀስ ይችላል። እኛ ልንቆጣጠረው የማንችለውን ነገር በእኛ ስሜት መፈረጅ አንችልም። የእኛ ማዘን የማንሸሽው እውነት ነው። ሞትን ግን ሞተን ስላላየነው ምናልባት ለእኛ አሳዛኝ ሞት ያልነው ለእነርሱ ደስታ ሊሆን ስለሚችል ኀዘናችን ውጤቱን ባለማወቅ (blindly) የሆነ ሆኖ ይገኛል። ይህንን ከመሬት ተነሥቼ አይደለም እየተናገርኩ ያለሁት። በአንድ ወቅት አባ መቃርስ የሞተ ሰው አጽም አገኘና በመቋሚያው ሲነካው ያ የሞተ ሰው ተነሣ። ከዚያ ቀድሞ ስለነበረው ነገር አብራራለትና። ከሞት ተነሥቶ በዚህ ዓለም እንዲኖር አባ መቃርስ ሲጠይቀው ያ ሟች ግን በዚህ ዓለም ከመኖር ሞት ይሻላል ብሎ ከሞት ተነሥቶ በዚህች ዓለም መኖርን አልወደደም። "ዕረፍተ ሞት ይኄሩ ሊተ እምጻዕራቱ ለዝንቱ ዓለም" እንዲል (መጽሐፈ መነኰሳት ፊልክስዩስ)። ክቡር ጠያቂ ሆይ በዚህ ዓለም መኖርን ከትልቅ ቁም ነገር ባይቆጥሩት ባይ ነኝ። እንዲያውም ከላይ የጠቀሷቸው አሳዛኝ ነገሮች ኀዘን የሌለበት ዓለምን እንዲመኙና ለዚያ ዓለም የሚያበቃዎትን ሥራ እንዲሠሩ ጉልበት ሊሆንዎት ይገባል ባይ ነኝ። ለዚያ ነውኮ ተወዳጁ ሐዋርያ "ኦ አኃውየ ኢታፍቅርዎ ለዓለም ወኢ ዘሀሎ ውስተ ዓለም። ዓለሙኒ ኀላፊ እስመ ኵሉ ኀላፊ ውእቱ" ያለ። በዚህ ዓለም ያለ

ሰው በማናቸውም መንገድ ሊሞት እንደሚችል ተረድተው እስካለ ድረስ ይውደዱት። ፈጣሪው በማናቸውም ሁኔታ ሲጠራው ደግሞ ይህ የእግዚአብሔር ሥራ ስለሆነ በተሻለችዋ ዓለም ያገናኘን ብለው ይጸልዩለት።

፰፬. አሁን ካለሁበት አካባቢ አንዲት ወጣት እኅት የሰባት ወር ነፍሰ ጡር ሁና ስትመረመር ልጁ በማሕፀንሽ ከቆየ አንቺ በሕይወት አትኖሪም ብለው ኦፐሬት አድርገው ልጁን አውጥተው ማሞቂያ ክፍል ለሁለት ወር ያክል አቆዩት ከዚያ በእግዚአብሔር ቸርነት እናት ከነልጇ ወደቤቷ ተመለሰች። እና ጥያቄዬ ልጁ ክርስትና የሚነሣው ከማሕፀን ከወጣበት ጀምሮ ነው ወይስ ዘጠነኛው ወር ከገባ በኋላ ያለው ነው የሚቆጠር?

መልስ፦ ማንኛውም ሰው ክርስትና የሚነሣው ከተወለደ ጀምሮ ባለው ቀን ወንድ ከሆነ በ40ኛው ቀን፣ ሴት ከሆነች በ80ኛው ቀን ነው። ስለዚህ ምንም እንኳ በሰባት ወራቸው ቢወለዱም ከተወለዱበት ጀምሮ ይቆጠራል ማለት ነው።

፰፭. ዲያቢሎስ በግእዝ የተጸለየን ጸሎት አይሰማም? ጸሎት በግእዝ አድርሱ አይሰማውም ይባላል። ልክ ነው?

መልስ፦ አይ ልክ አይደለም። ዲያብሎስ ሲክድ የተነሣው ቅድስናውን እንጂ ዕውቀቱን ኀይሉን አይደለም። ስለዚህ መንፈስ እንደመሆኑ የማንኛውንም ሰው ቋንቋ ያውቃል። በማንኛውም ቋንቋ በንጹሕ ልብ መጸለይ በእግዚአብሔር ዘንድ የተወደደ ነው። ቁምነገሩ ከቋንቋው ሳይሆን በንጹሕ ልብ መጸለዩ ላይ ነው።

፰፮. ተወልጄ ያደኩትበት አካባቢ ያሉ አንዳንድ ቄሶች የቅባት እምነት ተከታይ ናቸው። ነገር ግን ከተዋሕዶ ጋር ያለውን ልዩነት በደንብ አያውቁትም እንዲያውም በደፈናው የአባቶቻችን እምነት ነው ይላሉ። ቤተሰቦቼም የዚህ እምነት ተከታይ ናቸው። እኔ አሁን የምኖረው ሌላ አካባቢ ነው። የማምነውም የተዋሕዶን ሃይማኖት ነው። አልፎ አልፎ በዓመት ቤተሰብ ጥየቃ እሄዳለሁ አብሬ እበላለሁ እጠጣለሁ። አሁን ግን ያልጠበኩት ነገር ገጠመኝ። ይኸውም የሆነችን ልጅ ለትዳር ጠይቄያት በሁሉም ነገር ከተስማማን በኋላ የቤተሰቦቼን የቅባት እምነት ተከታይ መሆናቸውን ስትሰማ አይሆንም አለች። እኔም የእኔ እምነት ቅባት ካልሆነ (ተዋሕዶ ከሆነ) የቤተሰቦቼ የዚያ እምነት ተከታይ መሆን ችግር አይኖረው። ደግሞስ በየጊዜው ስለማንገናኝ ብየ ላስረዳት ብሞክርም ከቤተሰቦችህ ጋር አብሬ ልበላና ልጠጣ አልችልም አለችኝ። ይህንንም ጉዳይ የእርሷን ንስሓ አባት ብናማክራቸው ልጅቷ ትክክል ናት። በእምነት ከማይመስሉን ጋር አብሮ መብላት መጠጣት ክልክል ነው አሉ። ይልቁንስ አንተም ከቤተሰቦችህ ጋር አብረህ የምትበላ የምትጠጣ ከሆነ እንደተመለስህ አትቁጠረው አሉኝ። ከቤተሰቦቼ ጋር ግንኙነቴ በምን መልኩ ይሁን? ከልጅቷ ጋርስ?

መልስ፦ የተማረ ንስሓ አባት ያዙ የምለው በዚህ ምክንያት ነው። ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 51 ላይ "ብልህ መድኀኒት አዋቂ ካልተገኘ ድኅነተ ሥጋ እንደማይገኝ ሁሉ የተማረ ግብረ ገብ መምህረ ንስሓ ካልተገኘ ሥርየተ ኃጢአት አይገኝም" ይላልና። ስለዚህ አንተ የተዋሕዶ ሃይማኖት ልጅ በመሆንህ ከልጅቷ ጋር ተጋብታችሁ መኖር ትችላላችሁ። ከእናት ከአባትህ ጋር በሃይማኖት ብትለያዩም በማሕበራዊ ሕይወት ግንኙነት ግን እንቅፋት አይሆንም። በማሕበራዊ ሕይወት ከእስላሙም፣ ከጴንጤውም፣ ከቅባቱም፣ ከካቶሊኩም ከሌላውም ጋር አብሮ መኖር፣ በደስታና በኀዘን መገናኘት አልተከለከለም። የተከለከለው አብሮ መጸለይ፣ አብሮ ሥርዓተ አምልኮ መፈጸምና የመሳሰለው ነው። ስለዚህ አንተም አልፎ አልፎ ወደቤተሰብህ ስትሔድ አብረህ አትጸልይ፣ አብረህ ሥርዓተ አምልኮ አትፈጽም እንጂ በቤት ማደር፣ ሰላም መባባል፣ ምግብ ሲያቀርቡልህ ያቀረቡልህን ባርከህ መብላት ትችላለህ። ስለዚህ እጮኛህም ይህንን በመረዳት መዋደዱ ካለ ተጋብታችሁ ውለዱ ክበዱ ተዋለዱ።

፷፺. ታኅሣሥ 19 ቅዱስ ገብርኤል ሠለስቱ ደቂቅን ከእሳት ያወጣበት ቀን ነው ተብሎ በቤተ ክርስቲያናችን በድምቀት ይከበራል። የታኅሣሥ ወር ድርሳነ ገብርኤል ግን ስለ ሠለስቱ ደቂቅ ምንም ነገር አያወራም። ይልቁንስ የግንቦት ወር ድርሳነ ገብርኤል ነው የሚያትተው። ድርሳኑ በግንቦት በዓሉ ደግሞ በታኅሣሥ አይጋጭም? ድርሳነ ሚካኤል ደግሞ ሠለስቱ ደቂቅን ከእሳት ያወጣቸው ቅዱስ ሚካኤል እንደሆነ ያትታል። ይህንንስ እንዴት ያዩታል?

መልስ፦ ዙሮ ዙሮ መታሰቢያ በዓሉ መከበሩ እንጂ ቀኑ አይደለም። ሊቃውንት ቅዱስ ገብርኤል ሠለስቱ ደቂቅን ያዳነበትን መታሰቢያ ታኅሣሥ 19 እንዲከበር ሥርዓት ሠርተው እየተከበረ ይገኛል። መታሰቢያው ስለሆነ ነው በስንክሳርም "ተዝካረ በዓሉ" ተብሎ የተገለጸው። ግንቦት 19 ላይም ይህ መተረኩ መልካም ነው። ፍሬ ነገሩ በሁሉም ወራት ቢነገር እግዚአብሔር በቅዱስ ገብርኤል አድሮ የሠራውን ሥራ ማስታዎስና ማመስገኑ ላይ ነው። ሠለስቱ ደቂቅን ቅዱስ ሚካኤል አዳናቸው ቢባልም ይሆናል። ምክንያቱም ቅዱስ ሚካኤል መልአከ ምክሩ ለእግዚአብሔር ይባላልና። ስለዚህ የመዳናቸውን ምክር ማወቁን ለመግለጽ ሚካኤል አዳናቸው ይላል። በእሳቱ መካከል መገኘቱንና እሳቱን ማብረዱን ለመግለጽ ገብርኤል አዳናቸው ይላል። በሁሉም አድሮ የሚያድን እግዚአብሔር በመሆኑ ደግሞ እግዚአብሔር አዳናቸው ቢል ሁሉም ምሥጢሩ አንድ ነው።

፷፻. ስለ ርኩስ መንፈስ አወጣጥ ትክለኛው የቤተ ክርስቲያን ሕግ የቱ ነው? በቅዱሳን አባቶች እንደሚወጣ እርግጥ ነው። ርኩሳን መናፍስት በጥበብ ሊወጡ ይችላሉ? ሰው አስሮ ሊገዛቸው (ሊያዝዛቸው) ይችላል? ብዙ የቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት ይህ ሐሳብ ከሰሎሞን የመጣ ጥበብ ነው ይላሉ። እና እንደዚህ ዓይነት የጥበብ ሥራ ኃጢአት ነው?

መልስ፦ ርኩሳን አጋንንት በጥበብ መውጣት ይችላሉ። በምን ዓይነት ጥበብ ይወጣሉ የሚለውን ግን ለይተን ማወቅ አለብን። ጥበብ ሦስት ዓይነት ነው። ሥጋዊ ጥበብ፣ መንፈሳዊ ጥበብና ሰይጣናዊ ጥበብ ናቸው። አጋንንት ይወጣሉ ያልነው በመንፈሳዊ ጥበብ ነው። ይኸውም በመጾም፣ በመጸለይ፣ በመስገድ፣ ንስሓ ገብቶ ሥጋዉን ደሙን በመቀበልና በመሳሰሉት ይወጣሉ። ሰሎሞንም ቢሆን አጋንንትን አዘዘ አሠራቸው የተባለ በመንፈሳዊ ጥበብ እንጂ በሥጋዊ ጥበብ አይደለም። ስለዚህ በሰሎሞን እያሳበቡ በቤተክርስቲያን ስም እየነገዱ አጋንንታዊ ድግምትን እየደገሙ የሚያጭበረብሩ ሰዎች ስላሉ ከእነዚህ ሰዎች መራቅ አለብን። ታመን ከሆነ ለመፈወስ ወደሌላ ነገር መቀላዎጥ አያስፈልግም። ክርስቶስ በደሙ የመሠረታት ቤተክርስቲያን አለች ወደእርሷ መሄድ፣ ከሥጋው ከደሙ የሚበልጥ መድኀኒት ስለሌለ ንስሓ ገብቶ ዋናውን መድኀኒት ቁርባንን መቀበል ነው። በተጨማሪ ጠበል፣ መደበኛ የሕክምና ጣቢያዎች መሄድ እንጂ ወደሌላ መሔድ አያስፈልግም።

፳፱. አንዲት ሴት ለመጋባት ከፈለገች አንዳንዶች በ12 ዓመቷ ይላሉ ሌሎች ደግሞ 15 ነው ይላሉ። ሕገ መንግሥት ደግሞ 18 ዓመት እና ከዚያ በላይ ይላል። ይህ ነገር ከሕግ ጋር እንዴት ነው?

መልስ፦ አዎ በፍትሐ ነገሥቱ በምቶች ካደገች በ12 ዓመቷ፣ ያም ካልሆነ በመደበኛነት ሴት በ15 ዓመቷ ማግባት እንደምትችል ተገልጿል። ሕገ መንግሥቱ ደግሞ 18 ብሏል። ስለዚህ አንድ ሰው በቤተክርስቲያን ሕግ መሠረት የ15 ዓመቷን ቆንጆ አግብቶ ቢሄድና ሕገ መንግሥቱ ደግሞ አይፈቀድም ብሎ ቢያሥረው ቤተክርስቲያን ማስፈታት ይገባታል። መንግሥትም በውስጣዊ የቤተክርስቲያን ቀኖና ጉዳይ ጣልቃ መግባት የለበትም። ይህንን መቀየር ካስፈለገ እንኳ ሲኖዶስ ተወያይቶ የሚቀንነው ጉዳይ ነው።

፴. የዘወትር ጸሎት ላይ "ስብሐት ለአብ ስብሐት ለወልድ ስብሐት ለመንፈስ ቅዱስ ስብሐት ለእግዝእትነ ማርያም ድንግል ወላዲተ አምላክ ስብሐት ለመስቀል እግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ ክርስቶስ በምሕረቱ ይዘከረነ አመ ዳግም ምጽአቱ ኢያስተኀፍረነ ለሰብሖተ ስሙ ያንቅሐነ ወበአምልኮቱ ያጽንዐነ" ተብሎ "ለገቢረ ፈቃዱ ይደምረነ ሚካኤል ወገብርኤል ያውርዱ ምሕረተ በላዕሌነ ሱራፌል ወኪሩቤል ያስተምሕሩ ለነ በዕደ መልአኩ ይዕቀበነ" ተብሎ እግዝእትነ ማርያም አዕርጊ ጸሎተነ እየተባለ ይዘለቃል ብለዉ መምህሬ አስተምረውኛል። እንዴት ሳይጻፍ ሊጨመር ቻለ ብዬ ስጠይቅ በሊቃውንት የተጨመረ ነው ብለውኛል ሌሎች አባቶች ደግሞ ለዘአብልዓነ ዘንተ ኅብስተ ከተባለ በኋላ ሲያስገቡት እሰማለሁ። ስለዚህ ቃል ምን ይላሉ ያብራሩልኝ?

መልስ፦ የዚህ ጸሎት ደራሲ ማን እንደሆነ አልተገለጸም። በብዛት የተለመደው ከላይ በመጀመሪያ የተገለጸው ነው። ሆኖም ግን ቀጥለው ያሉ የጸሎት ክፍሎችም መልካሞች

ስለሆኑ እነዚህን ጨምረው የሚያስተምሩ መምህራን ካሉም የሚያስወቅስ አይደለም። ጸሎቱ መልካም ነውና። ስለዚህ ሁሉም እንደልምዱ መጸለይ ይችላል። የጸሎቱ ይዘት ሁለቱም ጥሩ ነውና።

**፸፩. ባልና ሚስት ቢኖሩና ሚስቱ ያለምንም ምክንያት ስለደበራት ብቻ ብትፈታው እሱ እንዴት ነው የሚሆነው ማግባት ይችላል ሁለተኛ?**

መልስ፦ ያለምንም ምክንያትማ አትፈታውም። ያው መነገር ያልተፈለገች የተደበቀች ምክንያት ትኖራለች። ስለዚህ መጀመሪያ ለመፋታት የማያበቃ ምክንያት ከሆነ በንስሓ አባት ማስመከር፣ እምቢ ካለች በሰበካ ጉባኤ፣ አሁንም እምቢ ካለች በወረዳ ቤተክህነት፣ አሁንም እምቢ ካለች በጳጳስ ማስመከር። ጳጳሱንም እምቢ ካለች እርሱ ልመንኩስ ቢል መመንኮስ፣ ላግባ ቢል ሌላ ማግባት ይችላል ተብሏል በፍትሐ ነገሥት ትርጓሜ።

**፸፪. አንዲት ሴት ውርጃ ቢከሰትባት በስንት ቀኗ ነው ቤተክርስቲያን መግባት የምትችለው? ለመግባትስ ቅድሚያ ምን ማድረግ አለባት?**

መልስ፦ በዚህ ዙሪያ የተጻፈ የሥርዓት መጽሐፍ አላገኘሁም። ነገር ግን ውርጃ ከተከሠተባት በኋላ የወለዱ ሴቶች እንደሚያጋጥማቸው ደመ ሕርስ (የአራስነት ደም) የሚቆይባት ከሆነ ሙሉ በሙሉ ከደም ነጻ እስክትሆን ትቆያለች።

**፸፫. አንዲት ሴት ጠበል በምትጠመቅ ሰዓት የወር አበባ ቢመጣባት ከጠበል ቦታ ሳትገባ ቤት አስመጥታ መጠመቅ ትችላለች? ካልቻለችስ እንዴት ነው ማድረግ ያለባት?**

መልስ፦ በዚህ ዙሪያም የተጻፈ ነገር አላገኘሁም። የጠበል ቦታ ቅዱስ ቦታ ስለሆነ ከዚያም የወር አበባ ሲያጋጥም፣ ወንዱም ዝንየት ሲያጋጥመው በዚያ ቀን ከዚያ ሄዶ ባይጠመቅ የሚል እይታ አለኝ። የመጠመቁም ጉዳይ የወር አበባው እስኪያልፍ እንዲሁ ጸሎት እየጸለይን ብቻ ብናሳልፈው እላለሁ።

**፸፬. አንድ ሰው በተከታታይ እየቀረበ ነገር ግን ለሰው ፍቅር ባይኖረው መጨረሻው ሲኦል ነው? ምክንያቱም ሁሉም ኖሮን ፍቅር ከሌለን ከንቱ ነንና።**

መልስ፦ በአንድ ጊዜ ለሰው ሁሉ ፍቅር አይኖረንም። ለሰው ሁሉ ፍቅር የሚኖረን ፍቅር ከሚባለው የቅድስና ደረጃ ላይ ስንደርስ ነው። ስለዚህ በተቻለን አቅም ንስሓ እየገባን፣ እየቆረብን፣ ሰውን ሁሉ ለመውደድ ጥረት እያደረግን እንኖራለን። መጨረሻችን ሲኦል ይሆን ገነት ግን የሚያውቀው እግዚአብሔር ብቻ ነው። እኛ ከእኛ የሚጠበቀውን እናድርግ። ሌላውን ለፈጠረን እንተወው።

**፸፭. ጊዜ የማልሰጠውን ልጅ መውለድ አልፈልግም። እግዚአብሔርን አትስጠኝ ብዬ መጠየቅ እችላለሁ? እንደ መቃወም አይሆንም?**

መልስ፦ እንዴት ያለ ጸሎት ነው ይህ ደግሞ?! ወልደህ ለልጅህ ጊዜ ካልሰጠህ ለማን ልትሰጥ ነው። ወልደን ልጆቻችንን በሚገባ ማሳደግ ራሱኮ አንዱ የጽድቅ መንገድ ነው። ከጽድቅ መንገድ አውጣኝ ዓይነት ጸሎት አይደረግም። ከዚያስ እንደቅዱሳን አበው ተወልዶ አንተን የማያገለግል ከሆነ እንዳይወለድ አድርገው ብሎ መጸለይ ጥሩ ነው። ስለዚህ ጊዜ መስጠት ግዴታህ ነው። እንዲህ ያለ ጅል ጸሎት አይደረግም። ለራስ ጥቅም ብለን ሌላውን መልካም ነገር አትስጠኝ አይባልም። ይህ ራስ ወዳድነት ነውና።

**፸፮. ሕፃናት መስቀል ሲሳለሙ እግዚአብሔር ይፍታህ ይበላል?**

መልስ፦ አዎ ይባላል። ምንም እንኳ ሕፃናት ኃጢአት ሊሠሩ ባይችሉም ሥርዓት የሚሠራ ለሁሉ ነውና። እኛ የማናውቀው እግዚአብሔር የሚያውቀው በደል ሊኖር ይችላልና።

**፸፯. ኅብስቱ ወደ ሥጋ መለኮት ወይኑ ወደ ደመ መለኮተ በየትኛው የቅዳሴ ክፍል ነው የሚቀየረው?**

መልስ፦ አይታወቅም። ይህንን የሚያውቀው እግዚአብሔር ብቻ ነው። ከመጀመሪያ ጀምሮ የታዘዘውን ጸሎት እኛ እንጸልያለን። መለወጥ የእርሱ ድርሻ ስለሆነ መቼ እንደሚሆን አይታወቅም። ዙሮ ዙሮ በቍርባን ሰዓት የምንበላው ሥጋው፣ የምንጠጣው ደሙ መሆኑን አምኖ መቀበል ነው።

**፸፰. አንድ ሰው ንስሐ ሳይገባ በሰማዕትነት ቢያርፍ ገነት ነው ወይስ ሲኦል ነው የሚገባው?**

መልስ፦ ገነትና ሲኦል የሚገባውን የሚያውቅ እግዚአብሔር ነው። በሰማዕትነት ማረፍ በራሱ ከመልካም ሥነ ምግባሮች አንዱ ነው። ይህንን እንናገራለን። ሲኦልና ገነት የሚገባውን የሚያውቅ ግን እግዚአብሔር ነው እኛ አናውቅም።

**፸፱. ዘፍ.18 ላይ "ጥቂት ውሃ ይምጣላችሁ። እግራችሁን ታጠቡ። ከዚህችም ዛፍ በታች ዕረፉ። እርጎና ወተትም ያዘጋጀውንም ጥጃ አመጣ። በፊታቸውም አቀረበው። እርሱም ከዛፉ በታች በፊታቸው ቆሞ ነበር። እነርሱም በሉ" ይላል። ይህን ንባብ አንዳንዶች ይዘው ሥላሴ በአብርሃም ቤት አልገቡም በውጪ ነው የተስተናገዱት ብለው ሲያስተምሩ ሰማሁ። ሐምሌ 7 ደግሞ ሥላሴ በአብርሃም ቤት የተስተናገዱበት ብለን እናከብራለን። ሥላሴ በአብርሃም ቤት አልገቡም ወይንስ ገብተዋል?**

መልስ፦ በእርግጥ መጽሐፍ ቅዱሱ መብላታቸውን እንጂ ከቤት ይግቡ አይግቡ የሚገልጽ ነገር የለውም። ነገር ግን በአዋልድ መጻሕፍት ገብተው እንደበሉ ተገልጿል። ስንክሳር የሐምሌ 7 የሚነግረንም ይህንኑ ጉዳይ ነው። ስለዚህ ከውጭ በሉ የሚሉት ሰዎች ያለምንም ማስረጃ በመሰለኝ ያቀረቡት ነው።

፹. እኛ አሁን የምቀበለው የጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ክቡር ሥጋ ቅዱስ ደም መለኮት የተዋሐደው ነፍስ የተለየው ነው ወይስ መለኮትም ነፍስም የተዋሐደው ነው?

መልስ፦ እኛ የምንቀበለው የክርስቶስ ሥጋና ደም መለኮት የተዋሐደው ነፍስ የተለየው ነው። ነፍስ የተዋሐደው ነው ከተባለማ በተፈተተ ቁጥር ይሰማዋል (ያመዋል) ባሰኝ ነበር። (ዕብራውያን ትርጓሜ)

፹፩. ማቴ.9 ላይ ፈሪሳውያን እሑድ፣ ማክሰኞ፣ ኀሙስ ይጾማሉና ይላል። ቀጥሎ ጾመ ረቡዕ፣ ጾመ ሰብዑ ጾመ ዐሡር አለና ይላል። ለምንድን ነው የሚጾሟቸው? ዛሬስ ይጾማሉ?

መልስ፦ ጾመ ሰቡዕ ጾመ ዐሡር ያለው እስራኤላውያን በሰባተኛው ወር በዐሥረኛው ቀን ማለትም ጥቅምት 10 የሚጾሙት ጾም ነው። እንዲሁም በዐሥረኛው ወር በጥር የሚጾሙት ነው (ዘሌ.23፥26)። ጾመ ረቡዕ ጾመ ኀሙስ የሚለው ደግሞ በሐምሌና በነሐሴ የሚጾሙት ጾም ነው (ዘካ.7፥5 ትርጓሜ፤ ኤር.52፥6-12)። ዛሬ አይሁዶች ይጹሟቸው አይጹሟቸው አላወቅሁም። የሚጾሙባቸው ምክንያቶች ግን ከጠቀስኳቸው ጥቅሶች ስለተገለጸ ከዚያ ይመልከቱ። በሳምንት ውስጥ እሑድ፣ ማክሰኞ፣ ኀሙስ የሚጾሙባቸውን ምክንያት ግን አላውቀውም።

፹፪. የካህን ሚስትና ካህናት መሸታ ቤት መሥራት ይችላሉ?

መልስ፦ ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 47 ላይ ክርስቲያኖች ወደ መሸታ ቤት መሄድ እንደሌለባቸው ተገልጿል። ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 24 ደግሞ መሸታ ቤትን ዲያብሎስ ምእመናንን የሚያሠግርበት ቤት ነው ብሎታል። ስለዚህ ምእመናን እንዳይሄዱ ከታዘዙበት ቤት ጭራሽ ሠራተኛ ሆኖ መግባት ያውም ደግሞ ካህንና የካህን ሚስት አይገባም። መሸታ ቤት የሚጨፈርበት፣ የሚሰከርበት ክፉ ቦታ ነውና።

፹፫. አንድ ሰው ልክ ሊቆርብ ቤተ መቅደስ ገብቶ የሠራው ግን ረስቶት ያልተናዘዘው ኃጢአት ትዝ ቢለው መቍረብ ነው ወይስ መተው ነው ያለበት?

መልስ፦ መጀመሪያ ንስሓ ሲገባ የተቻለውን ያህል አስታውሶ ይገባል። ከዚያ በኋላ ከንስሓ አባቱ ጋር መነጋገር ነው። "እኔ የማስታውሰውን ሁሉ ተናገርኩ ብዬ አስቤያለሁ። ምናልባት የረሳሁት ካለና ልቆርብ ስል ቢታወሰኝ ምን ላድርግ ብሎ ይጠይቃቸው" ቁረብ ካሉት መቍረብ ነው። የንስሓ አባቱ ባሉት መንገድ መመራት

ነው:: "ሳታውቅ በስሕተት እያወቅህ በድፍረት የሠራሃውን ኃጢአት ይቅር ይበልህ" ቢሉትም አንዳንድ የተረሣ ከባድ ቀኖና ሊያሰጥ የሚችል ጉዳይ ሊሆን ስለሚችል ከንስሓ አባቱ ጋር መክሮ ያድርገው::

፹፬. በታቦት፣ ወንጌል ሲነበብ፣ ተአምረ ማርያም ሲነበብ ጃንጥላ ይዘረጋል:: የምን ምሳሌ ነው?

መልስ፦ ይህ ትውፊት ነው:: ጃንጥላ የክብር መገለጫ ነው:: ድንግል ማርያም ለቅዱስ ኤፍሬም ስትገለጥ የብርሃን ድባብ ተዘርግቷል ተብሏል:: ይህ ክብሯን ያመለክታል:: ትውፊቱን በትውፊትነቱ አክብሮ መፈጸም ነው::

፹፭. ጃንጥላ ብዙ ጊዜ ከአንጸባራቂ ልብስ ይዘጋጃል አንጸባራቂነቱ ምስጢር ይኖረው ይሆን?

መልስ፦ በትውፊት እንደዚያ እየተሠራ ከዘመናችን ደርሷል:: የተለየ ምሥጢር ግን ይኑረው ወይም አይኑረው አላውቀውም::

፹፮. ጳጳስ ሳይገኝ ቤተክርስቲያን ማስመረቅ ይቻላል?

መልስ፦ በቤተክርስቲያን ምረቃ ጳጳስ ተገኝቶ ሜሮን መቀባት እንዳለበት ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 1 ላይ ተገልጿል:: ቤተክርስቲያን ስትከብርም ከእርሱ ጋር ሰባት ካህናት ይኑሩ ተብሏል:: በአተገባበር ግን በአንዳንድ ቦታዎች ሲደረግ ብንመለከትም በብዙ ቦታዎች ሲደረግ አናይም:: ምናልባት ሀገረ ስብከቱ በወከላቸው ሰዎች መከናዎን የሚችል ይሆን ወይም አይሆን እውቅናው የለኝም::

፹፯. የቅዳሴ ጊዜ ራሳችን ውኃ ይዘን ብንሄድስ ከቅዳሴ በኂላ መጠጣት እና ወደ ቤት መውሰድ እንችላለን

መልስ፦ በዚህ ዙሪያ የተጻፈ ነገር አላገኘሁም:: እና አላውቀውም::

፹፰. አንድ ሰው በልጅነቱ በተወሰነ መልኩ እንደ ነገረ ሃይማኖት፣ ነገረ ቅዱሳን ወዘተ የመሳሰሉ ኮርሶችን ተምሮ ከዚያ ሐዲስ ኪዳን ወይም ሌሎችን መጻሕፍት ጉባኤ ቤት ገብቶ ትርጓሜ ሳይማር ነገረ መለኮት ብቻ ተምሮ ሰባኬ ወንጌል መሆን ይቻላል?

መልስ፦ የነገረ መለኮት ትምህርት የራሱ የሆነ መሥፈርት አለው:: ያንን መሥፈርት አሟልቶ ከገባ አዎ ይቻላል:: የመጻሕፍት ጉባኤ ቤት የራሱ የሆነ የማስተማር ዘዴና ተማሪዎችን የሚቀበልበት መሥፈርት እንዳለው ሁሉ የነገረ መለኮት ዩንቨርስቲዎችም የራሳቸው የሆነ የማስተማር ዘዴና ተማሪዎችን የመቀበያ ዘዴ አሏቸው:: ከሁለቱም የሚሰጠው የእግዚአብሔር ቃል ነው:: ስለዚህ ከጉባኤ ቤትም ከመንፈሳዊ ኮሌጆችም የሚወጡትን ማክበር መልካሙን ትምህርታቸውንም መስማት ይገባል::

፹፱. ካህናት ቅዳሴ ለመግባት ከቤተልሔም ሲመጡ በግንባር መደፋት አለብን? አንድ አባት ልማድ ነው ተነሱ ሲሉ ሰማሁ። በቁርባን ጊዜስ በግንባር መደፋት አለብን? የሚቀመጥም አለ። ከሰገድንስ ሲገቡና በቁርባን ጊዜ መቸ ነው የምንነሣው?

መልስ፦ አዎ በቁርባን ጊዜም ገና ከቤተልሔም ወደ መቅደስ ሲገቡም በትውፊት እንሰግዳለን። ዙሮ ዙሮ ለእግዚአብሔር የቀረበ የአምልኮ ስግደት ስለሆነ ምንም ችግር የለውም። ከቤተልሔም ሲመጡ መቅደስ ከገቡ በኋላ መነሣት፣ በቁርባን ጊዜ ለአክብሮተ ሥጋ ወደሙ ከሰገድን በኋላ መነሣት እንችላለን።

፺. አንዳንድ ሰዎች ወደ ቤተክርስቲያን የጽጌ ረዳ አበባ መግባት የለበትም ይላሉ። ልክ ናቸው?

መልስ፦ አይደሉም። ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 17 ላይ እንደተገለጸው ጽጌረዳ ወደቤተ ክርስቲያን መባዕ ተደርጎ መሰጠት የሚችል ነው። "ወያብኡ ካዕበ ጽጌረዳ" እንዲል። ወደቤተ ክርስቲያን መባዕ ሆነው የሚገቡትን ሲዘረዝር ወይን፣ በለስ፣ ሮማን፣ እንኮይ፣ ሽቱና የመሳሰሉት ናቸው። ወደቤተክርስቲያን አስገብተው ሊጸልዩባቸው አይገቡም የተባሉ ደግሞ ሾላ፣ ሽንኩርት፣ ዱባ፣ ቅል ናቸው። በተለየ ወደ ሕንፃ ቤተክርስቲያን እንዲገባ የተፈቀደ ደግሞ ጽጌረዳ ነው። ሌሎቹ መባዕ ቢሆኑም ወደ ሕንፃ ቤተክርስቲያን ሳይገቡ ከውጭ ለበረከት እንበላቸዋለን ተብሏልና።

፺፩. ከስድስት ሰዓት እስከ ዘጠኝ ሰዓት መበላት የለበትም የሚሉ አሉ። ይህ አስተምህሮ ትክክል ነው?

መልስ፦ የጾም ወቅት ካልሆነ በስተቀር በሌላው ቀን ሰው በማናቸውም ሰዓት በልቶ እግዚአብሔርን ማመስገን ይችላል። አንድም እግዚአብሔርን አመስግኖ መብላት ይችላል። ለዚህ ፍንጭ የሚሰጡት ፍትሐ ነገሥትና ሃይማኖተ አበው ናቸው። ሃይማኖተ አበው ሕንፃ መነኰሳት ላይ "እስከ ስድስት እስከ ሰባት የሚጾምበት ጊዜ አለ" ካለ በኋላ ቅዳሜ ከቀዳም ሥዑር ውጭ እንደሌላው ቀን ቆይቶ መጾም እንደማይገባ ተገልጿል። ይህ ደግሞ እስከ ስድስት ይጾማል ካለና እስከ ዘጠኝ መጾም አይቻልም ካለ በመካከል መብላት እንደሚቻል ያመለክታል። መተርጉማንም ቅዳሜ ለእሑድ ምእመናን ከቤተክርስቲያን ስለሚያድሩ ጠዋት በልተው እንዳያድሩ ይርባቸዋል ማታ በልተው እንዳይገቡ ይጎራብጣቸዋልና አማካይ ሰዓት ላይ በስድስት ሰዓት በሰባት ሰዓት በልተው ይገባሉ ብሏል (ሃይ.አበ.20፥21 ትርጓሜ)። ፍትሐ ነገሥት አንቀጸ መነኰሳት ላይ ደግሞ የጉልበት ሥራ የሚሠሩ መነኰሳት በቀን ሁለት ጊዜ ይብሉ ካለ በኋላ አንደኛው ሰዓት 6፡00 ሰዓት ይሁን ብሏል (አንቀጽ 10)።

፺፪. የኖኅ ልጅ ካም የተረገመው እርግማን አሁን አፍሪካውያን ላለንበት ውጥንቅጥ ሕይወት እና ነጮች የበላያችን ለመሆናቸው ምክንያቱ ያ ሊሆን ይችላል?

መልስ፦ ሊሆን አይችልም። ካም የተረገመ በራሱ ኃጢአት ነው። የራስ ኃጢአት ለራስ ነው። በዘር ምክንያት የሚመጣ ርግማን በክርስቶስ ተሽሯል። በታሪክ ዓለምን አንቀጥቅጠው የገዙ ታላላቅ መሪዎች ከካም የተወለዱ ብዙ ናቸው። አሁን አሁን በአብዛኛው አፍሪካውያን በሥልጣኔ ወደኋላ ማለታችን ኋላቀር የፖለቲካ አካሄድ፣ ደካማ የሥራ ባህልና የመሳሰለው ስላለብን እንጂ ከካም ርግማን ጋር የሚገናኝ ነገር የለውም። ደግሞ ነጮች የበላያችን ናቸው ብሎ አእምሮን ማሳመን የበታችነት ስሜት ነው። ምንም በሥልጣኔ ቢበልጡን እኛም እነርሱን በብዙ መልኩ እንበልጣቸዋለን። ስለዚህ በእኩልነት ስሜት መኖር እንጂ በዝቅታ ሐሳብ መኖር አይገባም። አባቶቻችን በመንፈሳዊውም እንደነዝክሪ እንደነ ጳውሊ እንደነ እጨጌ በትረ ጊዮርጊስ እንደነያሬድ እንደነአባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ እንደ አድማሱ ጀንበሬ ልበ ሙሉ ሊቃውንት እንጂ የሚያንሱ አልነበሩም። በሥጋዊውም በጉልበት የመጣውን በጉልበት አንበርክከው የማረኩ ጀግኖች አርበኞችና ነገሥታት ልጆች ነን።

፺፫. በኦሪት በነበሩት ጻድቃን አባቶቻችን እናቶቻችን ስም ታቦት ቀርጸን በጸሎታቸው መማፀን እንችላለን? እንደዚያ ከሆነ ዮሐንስ አፈወርቅ ወኢይትከሃል ያቅርቡ ወኢምንተኒ ዘእንበለ በዐራቅይናሁ ለወልድ ይላልና እንደምን ይታያል?

መልስ፦ አዎ በኦሪት በነበሩ ቅዱሳን ታቦት ቀርጸን በስማቸው መማጸን እንችላለን። በሀገራችንም በአባታችን በአዳም፣ በነቢዩ ኤልያስና በመሳሰሉት አባቶች ስም ታቦት ተቀርጾ እግዚአብሔር እየተመሰገነበት ይኖራል። እንኳንስ አሁን በሐዲስ ኪዳን በዚያው በብሉይ ኪዳን ዘመን እንኳ ነቢዩ ኤልሳዕ በኤልያስ ስም ጸልዮ ረድኤትን አግኝቷል። የቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ሐሳብ ከጠቅላላው የነገረ ድኅነት ትምህርት አንጻር የተነገረ ነው። የሰው ልጆች ሁሉ የዳኑት፣ ልጅነት የተመለሰላቸው፣ ከመርገም የዳኑት ጌታችን መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀል ላይ ተሰቅሎ በፈጸመው የቤዛነት ሥራ ነው። በሐዲስ ኪዳን ሰው የሚድን ክርስቶስ በፈጸመው የቤዛነት ሥራ ሲያምን ነው። የእርሱን ቤዛነት ሳያምኑ መዳን ስለሌለ ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ወኢይትከሀል ያቅርቡ ወኢምንትኒ ዘእንበለ በዐራቅይናሁ ለወልድ ብሏል።

፺፬. ዓርብ የቀደሰ ሰው ተመልሶ ቅዳሜ ጠዋት የመቀደስ ኀላፊነት ቢኖርበት ዓርብ በ9:00 ሰዓት ተመግቦ እንዴት ነው 18:00 ሰዓት የሚሞላው?

መልስ፦ የቅዳሜ ቍርባን ከጠዋቱ 3:00 እንዲሆን ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 19 ትርጓሜ ላይ ተገልጿል። ስለዚህ ዓርብ የቀደሰ ሰው 9:00 ሰዓት ከበላ ከቀኑ የተረፈ 3:00 ሰዓት አለው። ከዚያ ሌሊቱ 12:00 ሰዓት አለ። ከዚያ ከጠዋቱ 3:00 ሰዓት አለ። እነዚህን ስንደምራቸው 3+12+3=18 ይሆናል ማለት ነው።

፺፫. የንስሓ አባት ጋ ባዶ እጅ አይኬድም ይላሉ። እንዲሁም ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በከተማ ያሉ ካህናት አባቶች ለንስሓ ልጆቻቸው የማይሆኑ ነገሮች እንዲያቀርቡላቸው ሲጠይቁ ይስተዋላል። ይህ ከቤተክርስቲያን አስተምህሮ ጋር እንዴት ይታያል? ሁሌም ስንሄድ መስጠት/ማድረግ አለብን?

መልስ፦ የንስሓ አባት ጋ ባዶ እጅ አይኬድም የሚለው አነጋገር ልማዳዊ አነጋገር ነው። በእርግጥ በብሉይ ኪዳን በእግዚአብሔር ነቢይ ፊት ባዶ እጅህን አትታይ ተብሎ ነበር (1ኛ ሳሙ.9፥7 ትርጓሜ)። በሐዲስ ኪዳን ግን አንድ ምእመን ወደ ንስሓ አባቱ ሲሔድ ለመናዘዝ፣ ቀኖና ለመቀበል ስለሆነ ባዶ እጁን መሔድ ይችላል። ምናልባት የንስሓ አባቴ ተቸግረዋል ብረዳቸው ብሎ በራሱ ፈቃድ መስጠት ይችላል። ግዴታ አድርግ የሚለው ሥርዓት ግን የለም። የንስሓ አባቶችም ከልጆች ይህንን ካላመጣችሁ እያላችሁ አታስቸግሩ። ይህ ብልግና ነውና። ከእግዚአብሔር በነጻ የተቀበላችሁትን ሀብት በነጻ መስጠት ይገባችኋል።

፺፬. ሁለት እጮኛሞች አሉ። ሁለቱም በጣም ይዋደዳሉ። በቤተ ክርስቲያን ሥርዓት ለመጋባት እና ለወደፊት ሕይወታቸውን በአግባቡ ለመምራት በሁሉም ነገር ቅድመ ዝግጅት በማድረግ ላይ ናቸው። እየተወያዩ እና እየተነጋገሩ ከስምንት ወር በላይ ቆይተዋል። እጮኛሞቹ የሚሠሩበት መሥሪያ ቤት የተለያየ ነው። በዚህ ሁኔታ እያሉ ግን አንድ ያልጠበቁት ነገር በልጂቷ በኩል አጋጠማት። እርሷ ከምትሠራበት መሥሪያ ቤት አንድ ልጅ አንቺን ካላገባሁ እሞታለሁ አላት። እርሷም እጮኛ አለኝ በቅርቡ ላገባ ነው ብትለውም አልሰማም እምቢኝ አላት። አግብታው ለመኖርም አትፈልገውም። እንዳትተወውም ሙቼ እገኛለሁ ብሏል። ደግሞ የእጮኛዋ ሕይወት ምን እንደሚሆን በጣም አሳስቧታል። ልጂቷም ምን ማድረግ እንዳለባት ግራ ገባት። ምን ይሻላል?

መልስ፦ ሌላ ልታገባ መሆኑን እያወቀ እርሷን ካላገባሁ እሞታለሁ ያለው ሰውዬ ውሸቱን ነው አትመኑት። ቢሞትም ይህ የራሱ ጉዳይ እንጂ ከልጅቱ ጋር የሚያገናኘው ነገር የለም። ስለዚህ እርሷ ከወደደችው ጋር ትጋባ። ያኛው እሞታለሁ እያለ የሚያስፈራራው ሰውዬም ቁርጡን አውቆ ሌላ እንዲያገባ ንገሩት። ይሄ ወንድ አሰዳቢ😁።

፺፭. "ለእሉ ክልኤቱ ፍጡራን ስብሐተ ፈጣሪ ይደልዎሙ" ይላል (መስተብቍዕ ዘመስቀል)። ምን ማለት ነው?

መልስ፦ ይህ ለቅዱስ መስቀልና ለእመቤታችን ለቅድስት ድንግል ማርያም የጸጋ ምስጋና እንደሚገባቸው የሚያመለክት ቃል ነው። ስብሐተ ፈጣሪ ይደልዎሙ የሚለው እርሱ በባሕርዩ እንደሚመሰገን እነርሱ ደግሞ በጸጋ መመስገን ይገባቸዋል ማለት ነው። ይህንን

የመሰለ አነጋገር በወንጌል ተጽፏል። ወልድ አብን እኔና አንተ አንድ እንደሆንን እነርሱም (ሐዋርያትም) ከእኛ ጋር አንድ ይሁኑ ብሏል። በወልድና በአብ መካከል ያለው አንድነት ባሕርያዊ ሲሆን በሐዋርያትና በአብ በወልድ ያለው አንድነት ግን የጸጋ ነው። የላይኛውም በዚህ አግባብ የተነገረ ነው።

፺፰. የቤተክርስቲያን መምህር ናቸው። ዕድሜያቸው 90ዎቹ ገብተዋል። እና አሁን በጻና ታመዋል። ትንሽ የሚቀምሱት ወተት ነው። አሁን ደግሞ ጾም ገባ እንዴት አናድርግ?

መልስ፦ በእርግጥ ፍትሐ ነገሥት አንቀጸ ጾም የታመሙ ሰዎች እንደሌላው የግድ እንዲጾሙ አያዝዝም። ስለዚህ የታመሙ የ90 ዓመት ሽማግሌ እንቢ ትሩፋቴ ይፈርስብኛል እጾማለሁ ካሉ እንዲጾሙ መተው ነው። አልቻልኩም ብለው ቢበሉም ይህ በደል አይሆንባቸውም። ቀኖና ፈቅዶላቸዋልና።

፺፱. እያወቀ ኃጢአት የሠራ ሰው ንስሓ ቢገባ ኃጢአቱ አይሠረይለትም ብለው ሲናገሩ ሰማሁ አንድ ካህን ትክክል ናቸው?

መልስ፦ አይደሉም። ሰው እያወቀ ኃጢአት መሥራት የለበትም። ነገር ግን በተለያዩ ምክንያቶች አውቆ እያለ ቢሠራም ንስሓ ከገባ ኃጢአቱ ይሠረይለታል። ካህናት ሲናዝዙን "ሳናውቅ በስሕተት እያወቅን በድፍረት የሠራነውን ኃጢአት እግዚአብሔር ይቅር ይበለን" የሚሉ ለዚህ ነው። ነገር ግን ኃጢአትን ልትሠሩ ስትሄዱ ልትሞቱ እንደምትችሉ አስባችሁ ብትሞቱ ደግሞ ይህ ሲኦል የሚያስገባ መሆኑን ተረድታችሁ መኖር ይገባል። አንድ መጽሐፍ ላይ አንድ ሰው ከአንዲት ሴት ጋር ዝሙት ሊፈጽም መጋረጃ ገልጦ ሲገባ እባብ ነድፎት እንደሞተ ተገልጿል። ስለዚህ ባለችን ጊዜ ምን መልካም ሥራ ሠርተን እንለፍ ብለን ተሻምተን የጽድቅ ሥራ መሥራት ሲገባን እያወቅን ወደ ጥፋት መሄድ ፈጽሞ አይገባም። እጠገናለሁ ብሎ መሰበር እንደማይገባ ሁሉ ንስሓ እገባለሁ እያሉ ኃጢአት መሥራትም አይገባም። ምናልባት የንስሓ ዕድሜን ሳናገኝ በዚያው ልንሞት እንችላለንና።

፻. የዘወትር ጸሎት ላይ "አንተ ውእቱ አምላከ-አማልክት ወእግዚአ-አጋእዝት ወንጉሠ-ነገሥት" ይላል። ከአንድ አምላክ ውጪ ሌሎች አማልክት አሉ?

መልስ፦ ሰማይንና ምድርን ፈጥሮ የሚያስተዳድር አምላክ እግዚአብሔር ብቻ ነው። እግዚአብሔር ግን ቸር ስለሆነ ለእርሱ የባሕርዩ የሆኑ ጉዳዮችን ለሰዎች ደግሞ በጸጋ የሚሰጥበት አግባብ አለ። ለምሳሌ በባሕርዩ ቅዱስ እግዚአብሔር ብቻ ነው። ነገር ግን ለሰዎች በጸጋ ቅድስናን ስለሰጠ ደጋግ ሰዎችም ቅዱሳን ይባላሉ። የእግዚአብሔር ቅድስና የባሕርይ የሰዎች የጸጋ በመሆኑ የእግዚአብሔርን ቅድስና ለመግለጽ ቅዱሰ ቅዱሳን ልንለው እንችላለን። ሰዎች ሌላውን ይገዙ ዘንድ በጸጋ አምላክ የሚሆኑበት ጊዜም አለ።

እግዚአብሔር ሙሴን "ናሁ ረሰይኩከ አምላኮ ለፈርዖን" ብሎታል (ዘፀ.7፥1)። ሰዎች የእግዚአብሔርን ሕግ ሲፈጽሙ የጸጋ አማልክት ይሆናሉ። ይህ አማልክትነታቸው ግን የጸጋ ነው። እግዚአብሔር ግን በባሕርዩ የእነዚህ ሁሉ አምላክ በመሆኑ አምላከ አማልክት ይባላል።

፻፩. የኢ-አማንያንን ጸሎት እግዚአብሔር ይቀበላል?

መልስ፦ እግዚአብሔርን ጠይቁት።

፻፪. አንድ ሊቀ ጳጳስ በዝሙት የወደቀን መነኩሴ ሥልጣን ማዳን ይችላል? ይህ ጉዳይ እኔ ባለሁበት ሀገር ላይ ሀገር ያወቀው ፀሐይ የሞቀው ጉዳይ ሆኖ እያለ የተበዳይን እውነተኛ ቃል ሰምቶ የተደረገውን ድርጊት ተነግሮት የመነኩሴውን ሥልጣን ሳይዝ ወደሌላ ሀገር ሂድ አገልግል ማለት ይችላል ሊቀ ጳጳሱ?

መልስ፦ ዝሙት የፈጸመ መነኮሴ ከክህነቱ ይሻራል። ይህ ደግሞ ቀኖና ነው። ቀኖናን ደግሞ አንድ ጳጳስ ብቻውን ማስተካከል አይችልም። ስለዚህ ጳጳሱ ይህንን ካደረጉ ልክ አይደሉም። ምናልባት ማስረጃ ጠፍቶ እርሳቸው ባደረጉት ማጣራት ምንም ፍንጭ ካላገኙ ደግሞ የሰዎችን ነገር ብቻ ሰምተው መወሰን ስለማይችሉ ጉዳዩን ለእግዚአብሔር ሰጥተው ቦታ ቀይረው ሊልኩት ይችላሉ። የተረጋገጠ ማስረጃ ቀርቦላቸው ወደሌላ ከላኩት ግን ልክ አይደሉም።

፻፫. አንዲት እህት ብታገባ ሚዜ የሆነቻትን ሴት ወንድሟ ማግባት ይችላል?

መልስ፦ የተከለከሉ የጋብቻ ዝምድናዎች የሥጋ ዝምድና፣ የክርስትና ዝምድና፣ የጋብቻ ዝምድና እና የአሳዳጊ ዝምድና ነው። ስለዚህ ሚዜዋ ከእነዚህ ከተጠቀሱት ዝምድናዎች ውጭ ከሆነች ያ ሰው ሊያገባት ይችላል።

፻፬. በዓለም ደረጃ የክርስትና ሃይማኖት የመከፋፈሉ ምክንያት የሰዎች ድካም ብቻ ነው? ወይስ መገለጡ ብዙ ጥያቄዎችን የማይመልስ ውስን በመሆኑ ነው?

መልስ፦ የሰዎች ደካማነትና ደካማነታቸውን አለመረዳታቸው ነው። እውነት ከእግዚአብሔር የሚገለጥና የተገለጠ ነው። የሰው ልጆች ግን በተገለጠው እውነት መኖር ሲያቅታቸው የራሳቸውን ልብ ወለድና መሰለኝ እየጨመሩ ከእውነታው እያፈነገጡ ከክርስትና እምነት እየወጡ የራሳቸውን መሰለኝ እምነት እያደረጉ ኖረዋል። መገለጡ የማይመልሰው ጥያቄ የለም። የእግዚአብሔር መገለጥ ሰው እስከመሆን የደረሰ ነው። ሰው ሆኖም አምላክነቱን አምላክ የሚያደርጋቸውን በማድረግ አስረግጧል። ስለዚህ ያፈረ ሰው ምንም ማስረጃ ቢቀርብለት አውቆ የተኛ ስለሆነ እንደማይቀበል ሁሉ የክርስቶስ መገለጥም ጭቃን ወፍ በማድረግ፣ ውሃን ወይን በማድረግ፣ ከሞት በመነሣትና

በተለያዩ አምላካዊ ሥራዎች የተገለጠ ቢሆንም ላለማመን የተኛ ሰው አያምንም። መገለጡ የማይመልሳቸው ጥያቄዎች የሉም።

**፻፯. ሳይገባው ጵጵስናን የተቀበለ በክህነቱ ዲቁናንና ቅስናን ቢሰጥ የተቀበሉት ክህነት ትክክል ነው ሊባል ይችላል?**

መልስ፦ በሕገ ወጥነት ጵጵስናን የተሾመ ሰው የእርሱ ክህነት ራሱ ተቀባይነት ስለሌለው የሚሾማቸው ሰዎች ክህነትም ተቀባይነት የለውም። ለምሳሌ ቅባቶች እንደዕቃ ዕቃ ጨዋታ ተሿሿሙና ጳጳስ ነን አሉ። አሁን እነርሱ ቢሾሙ ከእነርሱ የተሾመ ሰው ካህን ስላልሆነ መደፋፈር የለበትም። አሁን ላይ ራሱን መንበረ ሰላማ ብሎ ከተወገዘው ቡድንም ክህነትን መቀበል፣ መቁረብ፣ መጠመቅ አይገባም። ራሳቸውን መንበረ ጴጥሮስ ብለው የሰየሙና በሲኖዶስ ዕውቅና ሳይሰጣቸው አሁንም ጳጳስ ነን ብለው የሚሾሙ፣ የሚቀድሱ፣ የሚያጠምቁ የወሊሶ ተሿሚዎች ካሉም ክህነት የሌላቸው አጭበርባሪዎች ስለሆኑ ከእነዚህ መራቅ ይገባናል።

**፻፰. ብዙውን ጊዜ ሐሰተኛ አጥማቅያን ሲባል አሰማለሁ። ታዲያ ቅድስት ቤተክርስቲያን እውነተኛ አጥማቅያን ጸጋውን የሰጣቸው በዘመናችንስ የሉም ወይ?**

መልስ፦ ሲጀምር አጥማቅያን የሚባል የሥራ ወይም የአገልግሎት ዘርፍ በቤተክርስቲያን የለም። ስለዚህ አጥማቂ የምንከተልበት ምንም ምክንያት የለም። የልጅነት ጥምቀትን ለማጥመቅ ከሆነ ካህናት ሁሉ አጥምቀው፣ ቀድሰው ያቆርባሉ። ሰው ታሞ በጠበል ለመጠመቅ ደግሞ ራሱ ገብቶ ይጠመቃል እንጂ ሌላ አያስፈልግም። በውሃ ላይ እየጸለዩ በመርጨት ሰውን የመፈወስ ጸጋ ያላቸው ሰዎች ካሉ ደግሞ ሥራቸውን እንዳይገለጥ ከንቱ ውዳሴ እንዳይጥላቸው ራሳቸውን ሠውረው ይኖራሉ እንጂ እኛ ፈዋሽ ነን አይሉም። እንዲህ ያሉ አካላትም አጥማቅያን የሚባል ስያሜ የላቸውም። ሀብተ ፈውስ ለሁሉ የሚሰጥ አይደለም። ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ እንደተናገረው ሙት ከማስነሣት ይልቅ ንስሓ መግባት ይሻላል። ስለዚህ እንኳን ሙት የሚያስነሡ በሌሉበት ሙት እስከማስነሣት የሚደርሱ ተአምር አድራጊዎች ቢኖሩ እንኳ እኛም እነርሱን ከምንከተል ንስሓ ብንገባ ይበልጣል። እነርሱም ሙት ከሚያስነሡ ንስሓ መግባት ይሻላቸዋል። የአጥቢያህ ቤተክርስቲያን ሁሉ ነገር አላት። ከአጥቢያህ ቤተክርስቲያን መድኀኒት የሌለ ይመስል ከቦታ ቦታ መቀላወጥ አይገባም።

**፻፱. አንድ መነኰሴ ቄስ ወግዘታቸውን ሳይፈቱ ከዚህ ዓለም በሞት ተለዩ። ጥያቄው ወግዘቱን በሌላ ቄስ ማስፈታት ይቻላል ወይስ አይቻልም?**

መልስ፦ ይቻላል። ውግዘትን በተመለከተ ቄስ ያወገዘውን አውጋዡ ሳይሞት ሌላኛው ቄስ መፍታት አይችልም። ነገር ግን አውጋዡ ከሞተ በኋላ ቄስ ያወገዘውን ቄስ ይፈታዋል።

አውጋዡ ካልሞተ ደግሞ ቄሱ ያወገዘውን ኤጲስ ቆጶስ ይፈታዋል:: ኤጲስ ቆጶስ ያወገዘውን ጳጳስ ይፈዋል:: ጳጳስ ያወገዘውን ሊቀ ጳጳሳት ይፈታዋል:: አውጋዡ ካለም ከሞተም በኋላም ደግሞ ሊቀ ጳጳስ ያወገዘውን ጳጳስ አይፈታውም:: ጳጳስ ያወገዘውን ኤጲስ ቆጶስ አይፈታውም:: ኤጲስ ቆጶስ ያወገዘውን ቄስ አይፈታውም::

፲፰. የቤተክርስቲያን ልደት በበዓለ ጰራቅሊጦስ ነው & በዕለተ ዓርብ ነው የሚሉ መምህራን አሉና የትኛው ነው ትክክል?

መልስ፦ ሁለቱም ትክክል ነው:: ምእመናን ልጅነትን የሚያገኙበት ማየ ገቦ የፈሰሰ በዕለተ ዓርብ ስለሆነ በዕለተ ዓርብ ተወለደች ቢሉ ያስኬዳል:: እንደገና ደግሞ ምእመናን ሀብተ መንፈስ ቅዱስ በዝቶ የተሰጣቸው በጰራቅሊጦስ ስለሆነ ያን ጊዜ ነው ቢልም ይሆናል:: ሁለቱም ለምእመናን ሀብት የተሰጠባቸውን ጊዜ ለማመልከት የተነገሩ ስለሆኑ ያስኬዳሉ::

፲፱. በደቡብ ኢትዮጵያ በተለይ በጋርዱላ ዞንና በኮንሶ ባህል እህል ከተወቃ በኋላ ልክ ወደ ጎተራ እንደሚገባ እዚህ ደግሞ ጉድጓድ ይቆፈርና እዚያ ውስጥ ይቀበራል:: ማለት ጉድጓዱን ልክ እንደ ጎተራ ይጠቀሙታል:: አሁን አሁን ግን ሰዎች መጽሐፍ ቅዱስ ይከለክላል ይላሉ:: ይሄ ነገር እንዴት ይታያል?

መልስ፦ እህልን በጉድጓድ ማስቀመጥ ክልክል ነው የሚል መጽሐፍ ቅዱስ ላይ እስካሁን አላገኘሁም:: ይህን ለማለት ፍንጭ የሆናቸውን ጥቅስ ቢነግሩን መልካም ነበር:: ምክንያቱም መልእክቱ ለሌላ ሆኖ ቃል በቃል ወስደውትም ሊሆን ይችላልና:: ዙሮ ዙሮ የዓመት የሚሆነንን ምግብ በጎተራም ይሁን በሌላ እህልን የማስቀመጫ መንገድ ማስቀመጥ በደል አይሆንም::

፳. አቡነ ተክለ ሃይማኖት መጋቢት 24 ቀን እንደተፀነሱ ገድላቸው ይነግረናል:: አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስም መጋቢት 29 ቀን ነው የተፀነሱት:: ጥያቄዬ በዚያን ዘመን ይህ ወቅት የጾም ወቅት አልነበረምን? እና እንዴት እነዚህ ቅዱሳን አበው በጾም ወቅት ተፀነሱ?

መልስ፦ መጋቢት 24 ሁልጊዜ መጋቢት 29 ደግሞ ብዙ ጊዜ በዐቢይ ጾም ውስጥ ይውላሉ:: እነዚህ የከበሩ ታላላቅ አባቶቻችን በጾም ወቅት መፀነሳቸው የእነርሱን ቅድስና አይቀንሰውም:: እናት አባቶቻቸውም ደጋጎች እንደነበሩ ስለተገለጸ የእናት የአባቶቻቸውን ቅድስናም አይቀንስም:: ደጋግሜ እንደገለጽኩት ግንኙነት ኃጢአት የሚሆነው ዓርብ ረቡዕ፣ በሰሙነ ሕማማት ሲፈጸም ነው:: ሌሎች አጽዋማትንም ሰው ከግንኙነት ተከልክሎ ቢጾም ዋጋው ይበዛለታል:: ነገር ግን ከተጋቢዎች አንዱ የፍትወት ሐሳብ በሌሎች አጽዋማት ቢነሣበት ከምግቡ ወይም ከግንኙነቱ የፈለገውን ያስቀድም ተብሏል::

ሰዓቱንም ሲገልጽ ከቀኑ ዘጠኝ ሰዓት እስከ ምሽቱ ሦስት ሰዓት ባለው እንደሆነ ተገልጿል (ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 24 ትርጓሜ)።

**፻፲፮. አንድ ዲያቆን በአጋጣሚ እጁ ላይ ሰው ይሞታል ማለት ይገድላል። ክህነቱ ይቀጥላል? በኋላ ሲያገባስ በተክሊል ማግባት ይችላል?**

መልስ፦ ክህነትን ከሚያስሽሩ ኃጢአቶች አንዱ ሰውን መግደል ነው። ሰለዚህ ሰውን በመግደሉ ምክንያት ክህነቱ ይፈርሳል። ምናልባት ያለምንም መሣሪያ እግዚአብሔር ሆይ ፍረድ ብሎ ጸልዮ ጸሎቱ ተሰምቶ እግዚአብሔር ገድሎት ከሆነ ተጠያቂ አይሆንም። ቅዱስ ጴጥሮስ በጸሎቱ ሐናንያንና ሰጲራን በመግደሉ፣ ቅዱስ ጊዮርጊሰ በጸሎቱ ሰብዓ ነገሥታትን ማጥፋቱ በደል አልሆነባቸውም። በሰይፍ፣ በድንጋይ፣ በዱላ፣ ገፍትሮ በመጣል፣ መድኃኒት በመስጠትና በመሳሰለው የገደለ ካህን ግን ክህነቱ ይሻራል። የጋብቻው ሁኔታ ግን ድንግልናውን ከጠበቀ እንደማንኛውም ምእመን በተክሊል ሊያገባ ይችላል። የፈረሰበት ክህነቱ እንጂ ድንግልናው አይደለምና። የነፍስ ድንግልናው በመግደል ቢጠፋም በንስሐ ይመለሳል።

**፻፲፯. በሥርዓተ ቅዳሴ ጊዜ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን መንጦላዕት ዘግታ እንደምትቀድስ ይታወቃል። አንድ አንድ አድባራት ገልጠው ሲቀድሱ አይተን ለምንድን ነው ብለን ስንጠይቅ ከልጆቿ የሚሰወር ምሥጢር ስለሌለ ብለው መልሰውልናል። ሌላ የመጽሐፍ መምህርም ለወደፊቱ መከፈቱ እንደማይቀር እና ቢከፈትም ምንም እንዳልሆነ ነግረውናል። ልክ ናቸው?**

መልስ፦ ልክ ናቸውም ልክ አይደሉምም። በመጀመሪያ ይህ ጉዳይ ቀኖና በመሆኑ ከሀገር ሀገር አፈጻጸሙ ሊለያይ ይችላል። እንደሀገራችን ክርስቶስ ሲሰቀል ፀሐይ ጨረቃ ከዋክብት ብርሃናቸውን መሠወራቸውን ለመግለጽ መንጦላዕት (መጋረጃ) ተጋርዶ ይቀደሳል። በሀገራችን መንጦላዕት ጋርደን መጸለያችን ስለዚህ ነው። በሌሎች አብያተ ክርስቲያን ደግሞ ክርስቶስ ራቁቱን ተሰቅሎ ሰው ሁሉ በአደባባይ አይቶታል ብለው የምእመኑ እምነትና የትምህርት ደረጃም ከፍ ያለ ስለሆነ መንጦላዕት ከፍተው ይቀድሳሉ። ሃይማኖቱን ጠንቅቆ ለማያውቅ ሰው በመጋረጃ መሆኑ መልካም ነው። ለበቁት ግን ያለመጋረጃ ቢሆንም ነውርነት የለውም። ዙሮ ዙሮ ምእመናን ከትልቅ አዳራሽ ገብተን ዳቦ በልተን፣ ወይን ጠጥተን መጣን እንዳይሉ አምስቱን አዕማደ ምሥጢር በደንብ አስተምሮ እንዲያስቀድሱ ማድረጉ ላይ ትኩረት እናድርግ።

**፻፲፰. በኦሪት ወንዶች ሁሉ የሴት ቀሚስ ይለብሳሉ። ይህ ወንድ የሴትን ልብስ አይልበስ ከሚለው ትእዛዝ ጋር አይጋጭምን?**

መልስ፦ በኦሪት ወንዶች ሁሉ ቀሚስ እንደሚለብሱ ምንም ማስረጃ የለኝም። ነገር ግን በሀገራችንም እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ ወንዱ ይለብስ የነበረው እጀ ጠባብ የሚባል ቀሚስ ነበር። ምንም ቢሆን ግን በየዘመናቱ በየቦታው ሴቶች የሚለብሱት የሴቶች የሚባል ልብስ ነበረ አለ። የወንዶች የሚባልም እንዲሁ። ስለዚህ በየሀገሩ፣ በየባህሉ የሴት የሚባለውን ልብስ ወንድ እንዳይለብሰው የወንድ የተባለውን ልብስ ሴት እንዳትለብሰው ይህ ትእዛዝ ተነግሯል።

**፻፲፬. አንድ ሰው ያውም የእግዚአብሔር ካህን ድል ባለ ድግስ የጋብቻ ስንተኛ ዓመት በዓል እያሉ ማክበር ይችላሉ?**

መልስ፦ የጋብቻ በዓል የሚባል በዓል በቤተክርስቲያን ዕውቅና የለውም። ስለዚህ በዓል የሚለውን ስያሜ ከእንደዚህ ዓይነት ጉዳይ ማውጣት ይገባል። ነገር ግን አንድ ሰው ያገባበትን፣ የተወለደበትን ጊዜ አስቦ እስካሁን ያቆየውን አምላክ ማመስገን ይችላል።

**፻፲፭. ቅዱሳን (ጻድቃን) ከዚህ ዓለም ከተለዩ በኋላ ክብራቸው ይበላለጣል?**

መልስ፦ አዎ ይበላለጣል። ኮከብ ከኮከብ እንደሚበልጥ ሁሉ በዚህ ዓለም ብዙ ትሩፋት የሠሩ ባለመቶ ፍሬ ጻድቃን ከባለስልሳዎቹና ከባለ ሠላሳዎቹ በክብር ይበልጣሉ። ክብራችን እንደሥራችን ነው። ብዙ መልካም የሠራ ክብሩ የበዛ ይሆናል።

**፻፲፮. አንድ ዲያቆን ግራኝ ቢሆን ቅስና መሾም ይችላል?**

መልስ፦ በቀኝ እጁ መፈተት፣ ማጠን የሚችል ከሆነ አዎ መሾም ይችላል። በግራ እጅ አገልግሎትን መፈጸም አይገባምና።

**፻፲፯. አንድ አንድ ሰዎች የቅንድብ ጸጉር ሲላጭ ሙሉ ይሆናል እያሉ ይላጫሉ። እና መላጨት ይቻላል እንዴ? ማለት በእግዚአብሔር ዘንድ አያስጠይቅም?**

መልስ፦ ቅንድብን መላጨት በእግዚአብሔር ዘንድ እንደሚያስጠይቅ ወይም እንደማያስጠይቅ እስከዛሬ አላገኘሁም። ቅንድቡን የተላጨ ሰው ግን አይጥ ነው የሚመስል😁። የሆነ ሆኖ በሕክምና መላጨቱ አግባብ ሆኖ ካልተገኘ በስተቀር ለመዋብ ተብሎ ቀድሞ ያልነበረንን ሌላ መልክ መፈለግ ራሱ ፍትወት በመሆኑ በመልክህ ላይ መልክ አትጨምር ባለው አግባብ አለመላጨቱ መልካም ነው።

**፻፲፰. በሥራ ቦታም ሆነ በመንገድ ላይ ነዳያን ይለምናሉ። እና እኔ እየመረጥኩ ነው የምሰጠው። ለምሳሌ አቅመ ደካማ ለዓይነ ሥውር በአጠቃላይ ሮጦ መሥራት ለማይችል እሰጣለሁ። ሙሉ አካል ላለው ወጣት ግን አልሰጥም እናም አለመስጠቴ ያስጠይቀኛል?**

መልስ፦ በእርግጥ ተቸግሮ ለሚለምንህ ሰው ሁሉ መስጠት ይገባል፡፡ ልመና ከባድ ነው፡፡ የሰው ፊት ገርፏቸው በሰው ፊት እስከ መለመን ያደረሳቸው ቢቸግራቸው ስለሆነ ለሁሉም መስጠት ይገባል፡፡ ለሁሉም ለመስጠት አቅማችን የማይፈቅድ ሆኖ ከተገኘ ደግሞ መጀመሪያ ሃይማኖት ላላቸው መስጠት ይገባል፡፡ "አምጣነ ብነ ዕለት ንግበር ሠናየ ለኵሉ፡፡ ወፈድፋደሰ ለሰብአ ሃይማኖት" እንዲል (ገላ.6፥10)፡፡ እንደ ችግራቸው መጠን የበለጠ ለተቸገረው መስጠት ነውርነት የለውም፡፡ ይህ የርኅራኄ ሥራ ነውና፡፡

**፻፲፱. አንድ ሰው በየጸሎት ጊዜያቱ 36/36 ስግደት የሚሰገደው በግዝት በዓላትም ጭምር ነው ወይስ ይህ ከአምልኮ ስግደት አይመደብም?**

መልስ፦ ፍትሐ ነገሥት በሰባቱ የጸሎት ጊዜያት በየጊዜው 36 በጠቅላላው በቀን 252 ስግደት መስገድ እንደሚገባ ይናገራል፡፡ ይህ ስግደት የሚሰገደው ግን በጌታ በዓላት ከሆነ የወዲቅ ስግደት መስገድ ስለማይገባ በአድንኖ አንገትን ጎንበስ እያደረጉ ብቻ መስገድ ነው፡፡ በእመቤታችን በዓላት ግንባርን ከመሬት ሳያስነኩ የአስተብርኮ ስግደት መስገድ ነው፡፡ በሌላው ቀን ደግሞ የወዲቅ ስግደት መስገድ ነው፡፡ የአምልኮ ስግደት ቢሆንም ድካም እንዳይኖርበት ለጸሎት ስንጀምርና ስንፈጽም ከምንሰግዳቸው አራት ስግደቶች (መጀመሪያ 3 በኋላ 1 ወይም መጀመሪያ 1 በኋላ 3) ውጭ አይሰገድም፡፡ ነገር ግን ባሕታዊ ፈተና ቢበዛበት እሑድ ቀንም በሌሎች የከበሩ በዓላትም መስገድ እንደሚችል ወዝንቱ አንቀጽ ዘእንበለ ግዘት ተብሎ በፍትሐ ነገሥት ተገልጿል፡፡

**፻፳. አንድ ሰው ወይም ሕጻን አሐዱ ሲባል ካልነበረ ከእግዚኦታ በኋላ ገብቶ መቁረብ ይችላል? የማይቻል ከሆነስ የሚፈቀድበት ሁኔታዎች አሉ?**

መልስ፦ ቁርባን መቍረብ ያለበት ቅዳሴው ከጀመረበት ጀምሮ የነበረ እንጂ መካከል ላይ መጥቶ መቍረብ እንደማይገባ ሥርዓተ ቅዳሴ ይገልጻል፡፡ "ወዘኢነበረ በጥንተ ቅዳሴ ኢይቅረብ-ቅዳሴው ሲጀመር ያልነበረ አይቁረብ" እንዲል (ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 12)፡፡ የሚፈቀድበት አግባብ አለ፡፡ ለምሳሌ የታመመ ሰው ቤተክርስቲያን ከመግባት የሚከለክል በሽታ ቢገጥመው ከቅጽረ ቤተክርስቲያን ውጭ ሆኖ ካህኑ ሄዶ ሊያቆርበው ይችላል፡፡

**፻፳፩. በሰንበት ቀን መንፈሳዊ ጉዞዎች እንዴት ይታያሉ? ሰንበትን መሻር ወይስ መልካም ከማድረግ ይቆጠራል?**

መልስ፦ ድካም የሌለባቸው ረጅም ጉዞዎች ካልሆኑና የቅዳሴን ጊዜ የማያጥፉ ጉዞዎች ከሆኑ ምንም ችግር የለውም፡፡ ሰንበት የመንግሥተ ሰማያት ምሳሌ በመሆኗ ድካም ሊኖር አይገባምና፡፡ ድካም ያለበት፣ መንፈሳዊ ትምህርት የሌለበት፣ ቅዳሴ የሌለበት ጉዞ ከሆነ ግን ሰንበትን ከመሻር ይቆጠራል፡፡

፻፰፪. ንስሐ ለመናዘዝ ጧት ምግብ ሳይበላ ብቻ ነው ወይስ በማንኛውም ሰዓት ሠርክ (ምግብ ከተበላ) በኋላም ይቻላል? ቦታውስ? ግዴታ በቤተ ክርስቲያን ቅጽር ግቢ ብቻ ነው ወይስ በቤትም ይቻላል?

መልስ፦ በማናቸውም ቦታ፣ በማናቸውም ጊዜ፣ በማናቸውም ሁኔታ ንስሓ መግባት ይቻላል። ከበላ በኋላም በድሎ ከሆነ በደሉን ማሳደር ስለሌለበት ለንስሓ አባቱ መንገር ይችላል። የንስሓ አባቱ ቤተክርስቲያን ከሌለ ከሰፈራቸው ሄዶ መንገር ነው።

፻፰፫. አንዳንድ ካህናት ጾም እስከ ስድስትና ሰባት ሰዓት ይበቃል። እግዚአብሔር ምን ሠራችሁ እንጂ ምን በላችሁ/በስንት ሰዓት በላችሁ አይልም ይላሉ ለምዕመኑ። ምዕመኑ ምን ያድርግ?

መልስ፦ እንደዚህ የሚባል አስተምህሮ የለም። እነቂሴ የሚቀንኑት የግል ቀኖና የለም። አባቶቻችን ቅዱሳን ሠለስቱ ምእት የጾም ጊዜ እስከ ቀኑ 9:00 ሰዓት እንዲሆን ሥርዓት ሠርተዋል። ስለዚህ በሥርዓቱ መመራት እንጂ የራስን ቶሎ የመብላት ፍላጎት በሌሎች ለማሳደር ያልተባለን ማለት አይገባም።

፻፰፬. አንድ ሰው በሥጋ ደዌ ተይዞ ወይም መሻቱ ይፈጸምለት ዘንድ አንድ ቤተክርቲያን ተሳለ ቢጠብቅ ለውጥ አጣ። ከዚያ ከሌላ ቤተክርስቲያን ተሳለ። እግዚአብሔር ባለው ጊዜ ፍላጎቱ ቢሆንለት ስለቱን ለየትኛው ይስጥ?

መልስ፦ መጀመሪያ ስትሳሉ ቤተክርስቲያን አንዲት መሆኗን ተረድታችሁ ተሳሉ። ይህንን ሳትረዱ የምትሳሉት ስለት ጥቅም የለውም። በሁሉም ቤተክርስቲያን የሚመለከው አንድ እግዚአብሔር ነው። ቢሆንም ግን እናንተ ደግሞ ለይታችሁ ለዚህ ቤተክርስቲያን እሰጣለሁ ካላችሁ ለተናገራችሁት መስጠት ነው። ቃል ኪዳን ላይ ለራሳችሁ ቃልም መታመን አለባችሁና።

፻፰፭. ሰው ሲሞት ጥይት የሚተኮስበት አካባቢ ላይ አጥቢያዎች በተናጠል እንዳይተኮስ ይከለክላሉ። ከአንዳንድ አጥቢያ ካህናት ለፍትሐት እስኪመጡ/እስኪጀምሩ ችግር የለውም በሌላው ደግሞ በቃ ነፍስ ከተለየች ጀምሮ ይከለከላል። በመሐል አፈንጋጭ ዘመድ አሊያ ምቀኛ ሲተኩስ ጥለው ይሄዳሉ ወይም አይመጡም። እዚህ ላይ መጠየቅ የፈለኩት በቋሚዎች ስሕተት የሞተች ነፍስ ለምን ትቀጣ?

መልስ፦ ሲጀምር በሰርግ ጊዜ፣ በልቅሶ ጊዜ ጥይት መተኮስ ኋላቀርነት ነው። ካህናት ይህንን ኋላቀርነት በምክር ለማስተካከል ሲሞክሩ ሕዝቡ አልሰማ ሲላቸው እንግዲያውስ አንፈታም ብለው ይሄዳሉ። ሕዝቡም ይህንን በመፍራት አሁን አሁን እየተወ ነው። ዙሮ ዙሮ ግን ጥይት መተኮስን ማቆም ይገባል። ፍትሐቱንም ማድረግ ይገባል።

፻፰፮. አንድ ዲያቆን ለማግባት ከሴቷ በስንት ዓመት መብለጥ አለበት?

መልስ፦ በዚህ ዙሪያ የተቀመጠ የዕድሜ ገደብ የለም:: ብቻ የእርሱ ዕድሜ ከ20 ዓመት የእርሷ ዕድሜ ከ15 ዓመት በላይ ሊሆን ይገባል::

፩፳፯. ካህናት ሲያጠፉ ተዉ የሚሉትን ጥቅስ እየጠቀሱ ካህናትን አትውቀሱ ተብሏል እያሉ ምእመኑን ዝም የሚያሰኙ አሉ:: ትክክል ነው ወይ?

መልስ፦ ጥፋታቸው ቤተክርስቲያንን በብዙ መልኩ የሚጎዳ ከሆነ ካህናትንም መገሠጽ ይቻላል:: ከጥፋታቸውም እንዲመለሱ ተዉ ማለት ይገባል:: ዐመፀኛ ከሆነ ግን እንኳንስ ቄስን ጳጳስንም ተው ማለት እንደሚገባ ሐዋርያት በግጽው ሲኖዶስ "በእንተ ዐመፃሁ ኢያፍርህከ ጽጽስናሁ" ብለዋል (ትእዛዝ 25):: ነገር ግን ቤተክርስቲያን የማይጎዳ የግል ችግር ከሆነ በግል መንገር ይገባል እንጂ በአደባባይ ኃጢአቱን መዘርዘር አይገባም::

፩፳፰. ድርሳነ ሚካኤል ላይ የሚጋቡና የሚወልዱ ሰዎችን የሚመስሉ አጋንንት አሉ ይላል:: አጋንንት ጾታ አላቸው?

መልስ፦ አጋንንት ሁለት ዓይነት ናቸው:: አንደኞቹ ረቂቃን አጋንንት ናቸው:: ረቂቃን አጋንንት ደግሞ ምንም በክፋታቸው ከመዓርጋቸው ቢወርዱ መላእክት ናቸው:: የመላእክት ደግሞ ጾታ የላቸውም:: "ወመላእክትሰ መንፈሳውያን እሙንቱ እለ እንበለ ሥጋ ወአልቦ ላዕሌሆሙ ሞት ወድካም ወትድምርት ከመ ሰብእ ለተዋስቦ:: ወአልቦ ላዕሌሆሙ ግዕዘ ሰብእ በዘይትዋለዱ ወአልቦ ላዕሌሆሙ ግዕዘ ተባዕት ወአንስት" እንዲል (ድርሳነ ሚካኤል):: ሁለተኞቹ ልቡሳነ ሥጋ አጋንንት የሚባሉት ግን በሰው ሥጋ አድረው ወይም የሰውን ሰውነት ተዋርሰው የሚኖሩ አጋንንት ናቸው:: ይወልዳሉ ይዋለዳሉ የተባሉት እነዚህ ልቡሳነ ሥጋ አጋንንት ናቸው::

፩፳፱. በተመሳሳይ ጾታ መካከል ከልክ ያለፈ ወዳጅነት ተገቢ ነው? አንዳንድ ሰዎች ሁኔታቸው (የሚያደርጉት ነገር መተቃቀፍ፣ መሳሳም፣ መላፋት) ስናየው ግን የግብረ ሰዶም ይመስላል እናም ያስፈራሉ:: እረፉ ስንል ዳዊትና ዮናታን እንደ ነፍሳቸው ይዋደዱ ነበር ይሉናል:: ለእንደ እነዚህ ዓይነት ሰዎች ምን ብናደርግ ይሻላል?

መልስ፦ ዳዊትና ዮናታን ይዋደዱ ነበር የሚለው በእግዚአብሔር ፍቅር እንጂ በፍትወታዊ ፍቅር አይደለም:: የተመሳሳይ ጾታ ፍትወታዊ ፍቅርማ በድንጋይ አስወግሮ እንደሚያስገድል ራሷ ኦሪት ትናገራለች:: ስለዚህ ዳዊት ዮናታንን ዮናታን ዳዊትን ይወደው ነበር ማለት በዳዊት ክፉ ነገር እንዳይደርስ ዮናታን ይከላከልለት ነበር ወይም ዳዊት መልካም ነገርን እንዲያገኝ ይመኝለት ነበር ማለት ነው እንጂ ሌላ ትርጉም የለውም:: ስለዚህ በተመሳሳይ ጾታ መካከልም በተቃራኒ ጾታ መካከልም ፍትወታዊ የሆነ መሳሳም፣ መተቃቀፍና መላፋት ልክ አይደለም::

፲፴. ጽዋዕ በተመለከተ ሴቶች የቅዱስ ሚካኤልን ወንዶች የእመቤታችንን ጽዋዕ መጠጣት ይችላሉ?

**መልስ፦ አዎ ይችላሉ።**